# በፍትሐ-ብሄር ጉዳዮች ክርክር ሂደት በፍ/ቤት የሚሰጡ ቀጠሮዎች ምክንያታቸውና የተከራካሪ ወገኖች አለመቅረብ የሚያስከትለው ውጤት በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፡- ሕጉና አተገባበሩ

**ተዋቸዉ ሞላ♣**

**Abstract**

*Obviously, when the aggrieved party pleads his/her case before courts, the later usually renders several adjournments to perform various tasks in a given case in which the non-appearance of parties has an adverse effect on their constitutional rights. From several years until now, there is divergence before courts in Ethiopia, over the purpose of adjournments and effect upon non-appearance of one or both parties in a civil suit. Therefore, this article aimed to clarify the disagreement between adjournments in terms of purpose and their effects upon non-appearance of one or both parties in Ethiopia. The doctrinal research type and qualitative method of study was followed. Accordingly, the author finds; first, to pass a valid judgment on a given case a civil bench is expected to render five types of adjournments with different function on each category. Second, as the court's function on each adjournment category is different, the effect upon the absentee(s) party on each adjournment is also different. This includes losing the right to be heard in writting, leading to either ex-parte proceeding, striking-out or dismissal of the suit as well as losing the right to evidence a claim by submitting witnesses testimony. The author concludes the function of court on each adjournment and effects upon non-appearance of the party(s) are different. Consequently, courts should duly and diligently perform functions of each adjournment to avoid delay, injustice, and be restrained from passing arbitrary penalty upon the absentee(s) party.*

**Keywords:** Adjournment, Civil Litigation, Courts, Parties Non-Appearance, Ethiopia Civil Procedure Law.

♣ በህግ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የህግ ት/ቤት መምህር/ሌክቸረር/።የኢ-ሜል አድራሻ tewachewmolla3971@gmail.com

## አህጽሮት-ጽሑፍ

*ዜጎች ፍትሕ ለማግኘት ቅሬታቸዉን ለመደበኛው ፍ/ቤት ሲያቀርቡ መደበኛዉ የግጭት አፈታት ሂደት የሚከተላቸው ሥነ-ሥርዓቶችን የማክበር ግዴታ አለባቸዉ። ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው ሥነ-ሥርዓት የቀጠሮ ጊዜ ማክበር ነው። ለብዙ ጊዜ በሀገራችን ፍ/ቤቶች በቀጠሮ አሰጣጥ እና ክንዋኔዎቻቸዉ እንዲሁም የተከራካሪዎቹ አለመቅርብ ስለሚኖረዉ ዉጤት አጨቃጫቂ ከመሆኑም በላይ በፍ/ቤቶችም ወጥነት የጎደለዉ ልምድ ሲስታዋል ቆይቷል፤ ይስተዋላልም። ይህ ደግሞ በዜጎች ሕገ-መንግሰታዊ መብቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል። ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነዉ ይህ ችግር ሲሆን በፍትሐ-ብሄር ችሎት የፍ/ቤት ቀጠሮ ትርጉም እና ክንዋኔ እንዲሁም ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ወይም ሁለቱም ቀጠሮ አክብረው አለመገኘታቸው የሚያስከትለውን ውጤት ግልጽ በማድረግ በዜጎች ላይ የሚደርሰዉን አሉታዊ ተፅዕኖ መቅረፍ አስፈላጊነቱን በማመን ነዉ። ለዚህ ጽሁፍ ዝግጅት መጽሐፍትን፣ ሕግጋትንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዎችን ጸሀፊዉ ዳስሷል። በዚህ ጥናት የመጀመሪያዉ ግኝት በሕግ ማዕቀፉ ፍ/ቤት በተያዘው የክስ ጉዳይ አስፈላጊውን ክንውን ለማድረግ አምስት አይነት ቀጠሮ ሊሰጥ እና በእያንዳንዱ ቀጠሮም የተለያየ ክንዉን እንደሚያደረግ ያሳያል። ሁለተኛዉ ዋና ግኝት ፍ/ቤት በተለያየ ቀጠሮ የሚከናወነዉ ተግባር መለያየቱን ተከትሎ ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱ ባይቀርቡ ሊከተሉ የሚችሉት ውጤቶች የተለያዩ ናቸው ። እነዚህም የተከሳሽ የጽሑፍ መልስ የማቅረብ መብት መታለፍ፣ በሌሉበት የክሱ መሰማት መቀጠል፣ የመዝገብ መዝጋት፣ የክስ መዘጋት እና ማስረጃ የማሰማት መብት መታለፍ ናቸዉ። ሕጉ የፍ/ቤት ቀጠሮና ክንዋኔ እንዲሁም ባልቀረቡ ተከራካሪዎች ላይ የሚወሰደዉ እርምጃን በሚመለከቱ አንዳንድ ድንጋጌዎች ላይ ግልፅነት የጎደለዉ እና በቂ አለመሆኑ እንዲሁም በሕጉ እና በአተገባበሩ መካከል ልዩነት መኖሩ ሌላዉ ችግር ነዉ። ስለዚህ ፍ/ቤቶች ለፍትሕ ሲባል በያዙት ቀጠሮ የሚተገብሩት ክንዋኔና ባልቀረቡ ተከራካሪዎች ላይ የሚከተለዉ ዉጤት የሕጉ ዓላማና ይዘትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።*

---

**መሪ ቃላት፡** ቀጠሮ፣ የፍትሐብሄር ክርክር፣ ፍ/ቤት፣ የተከራካሪዎች በቀጠሮ አለመቅረብ፣ የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ

---

## 1. መግቢያ

ሕግጋት በአጠቃላይ ይዘታቸዉ መሠረታዊ ሕግ (Substantive laws) እና የሥነ-ሥርዓት ሕግ (Procedural laws) ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። የሥነ-ሥርዓት ሕግ በበኩሉ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት እና የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተብሎ ይከፈላል። አንዳንዴም የማሥረጃ ሕግ እንደ ሦስተኛ ክፍል ይታያል። መሠረታዊ ሕግጋት የሚባሉት የሰዎችን መብትና ግዴታ የሚደነግጉ ሲሆን፤ የሥነ ሥርዓት ሕጎች ደግሞ ጥሰት ሲያጋጥም እነዚህ መብትና ግዴታዎች ሕግን ተከትለው የት እና እንዴት ሊተገበሩ እንደሚገባ አቅጣጫ ይጠቁማሉ።[1]

የሥነ-ሥርዓት ሕግ ዜጎች በመሠረታዊ ሕግ የተደነገገዉን መብታቸውን ለማስከበር የትና እንዴት እንደሚሄዱ እንዲሁም ክአቤቱታ አቀራረብ ጀምሮ እስከ መጨርሻው ደረጃ (ዉሳኔ እና አፈፃፀም ድረስ) በሚኖረው ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡ የሥነ-ሥርዓት ደንቦችን የሚደነግግ ነው። የሥነ-ሥርዓት ሕግ ብቻዉን የሚቆም ሳይሆን መሠረታዊ ሕግጋት ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል "[ዓ]ላማዉም የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ ዉሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ (...) በመሆኑ (...) እጅግ ጠቀሜታ ያለዉ ነዉ"።[2] የሥነ-ሥርዓት ሕጎችን ማወቅ እና አለማወቅ እንዲሁም ማክበርና አለማክበር በሕግ የተሰጠንን መብት እና ግዴታ መጠቀም እንደመቻልና አለመቻል ያህል ነው።[3] "የአንድን ክርክር ዉጤት ከመሠረታዊ ሕግ ልዩነት ይልቅ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግና አተገባበር ልዩነት በበለጠ እንደሚለዉጠዉ በዘመናችን ግንዛቤ ያገኘ ጉዳይ ነዉ።"[4]

---

[1] Robert Allen Sedler, *Ethiopian Civil Procedure Law* (Faculty of Law Haile Selassie I University in association with OUP, 1968) 1, Para.1. [Here in after Sedler].

[2] አበበ ሙላቱ, 'የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረታዊ ችግሮች' (የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረታዊ ችግሮችና ማሻሻያዎቹ ላይ ያተኮረ ኮንፈረንስ, ዓለማየሁ ሃይሌ መታሰቢያ ድርጅት, 1998 ዓ.ም) 12. [ከዚህ በኃላ አበበ በማለት ተጠቅሷል]; Stuart Sime, *A Practical Approach to Civil Procedure* (10th edn, OUP, 2007) 165, Para. 12.01.

[3] Jack S. Emery and others, *Civil Procedure and Litigation: A Practical Approach*(West Legal Studies, Thomson Learning, 2000) 1.

[4] አበበ 12.

የሥነ-ሥርዓት መብቶች እንደ መሠረታዊ ሕጎች በሕገ-መንግሰቶችና አለምአቀፍ ኮቬናንቶች ታቅፈዋል፡፡[5] የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ) የተለያዩ የሥነ-ሥርዓት መብቶችንና ግዴታዎችን ይዘረዝራል፡፡ ነገር-ግን ተግባራዊነቱ ተቋማዊና የሕጉ ችግር ተብለዉ የሚከፈሉ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች እንዳሉበት ተተንትኗል፡፡[6] ተቋማዊ ችግር የሚባሉት የማብራሪያዎችና የዝርዝር ደንቦች አለመኖር፣ የአስፈፃሚ ተቋማት አለመቋቋም፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉን ለማሻሻል አለመቻል፣ የፍ/ቤቶች ሚና ጎልቶ አለመዉጣት፣ የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት አብረዉ አለመተግበራቸዉና አስተዳደራዊ ችግሮች ናቸዉ፡፡[7] በሌላ በኩል ከሕጉ የሚመነጩ ችግሮች የአማረኛዉ ቅጅ ከእንግሊዘኛዉ ጋር አለመጣጣም፣ ሕጉ ሲቀዳ የተዘለሉ ወይም ያላግባብ የተጨመሩ ደንቦች መኖር፣ የአቤቱታ አቀራረብን በሚመለከት (የፍ/ቤቶች ተሣትፎ፣ የክስ አቤቱታ ምክንያት ሁኔታ፣

---

[5] የኢትዮጵያ ፌድራላዊና ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 1/1987 ቁጥር37 (1) *“ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉ ማንኛዉም ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ፡፡”* ቁጥር25 *“ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸዉ”; African Charter on Human and Political Rights (ACHPR)* 1981, *Article 7(1) “Every individual shall have the right to have his case heard. This comprises: (a) the right to an appeal to competent national organs against acts violating his fundamental rights as recognized and guaranteed by conventions, laws, regulation and customs in force; (b) the right to be presumed innocent until proved guilty by a competent court or tribunal; (c) the right to defense, including the right to be defended by counsel of his choice; (d) the right to be tried within a reasonable time by an impartial court or tribunal;* The Universal Declaration of Human Rights (UDHR) 1948, Article 8 *“Everyone has the right to get an effective remedy by the competent national tribunals for acts violating the fundamental rights granted him by the constitution or by any other law” በማለት ይደነግጋል;* International Convention on Civil and Political Rights (ICCPR) 1966, Article 2(3) *“Any person whose rights or freedoms as herein recognized are violated shall have an effective remedy.and “any person claiming such a remedy shall have his right thereto determined by competent judicial, administrative or legislative authorities or by any other competent authority(...).*” Article 10 *“Everyone in full equality to a fair and public hearing by an independent and impartial tribunal in the determination of his rights and obligations and of any criminal charge against him.*” And as it is provided under articles 9, and 14 of ICCPR such rights applies to civil and criminal proceeding. ኢትዮጵያ የአለምአቀፍ የሰባዊና ፖለቲካዊ መብቶች ኮቬናንትን አፅድቃለች እንዲሁም የአፍሪካ የሰባዊና ፖለቲካዊ መብቶች ኮቬናንት እና የ1948 የተባበሩት መንግሰታት ጠቅላላ ጉባኤ ዩኒቨርሳል ዲክላሬሽንስ ኦፍ ሂዩማን ራይትስ አባል መሆኗ ይታወቃል፡፡

[6] አበበ 16-50.

[7] ዝኒ ከማሁ 16-29.

የአቤቱታ አይነቶችና የአቤቱታ ማሻሻል ሁኔታ)፣ ስለ ጣልቃ ገብነት፣ ፍትሕ የማግኘት መብት፣ የማስረጃ አቀራረብና በይግባኝ ጊዜ የሚታዩ ችግሮችን እንደሚያጠቃልል ተመላክቷል፡፡[8]

በመደበኛው የግጭት አፈታት ሂደት ፍ/ቤት ከሚከተላቸው *ሥነ-ሥርዓቶች* ውስጥ አንደኛው የቀጠሮ ጊዜ መስጠት ነው፡፡ ይህ ጽሑፍ በዚህ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ሲሆን ሕጉንና አተገባበሩን መተንተንና ሕጉ በጉዳዩ ላይ ያለዉን በቂነት (adequacy) መገምገም ነዉ፡፡ ብዙዉን ጊዜ በሀገራችን ባሉ ፍ/ቤቶች በቀጠሮ አሰጣጥ እና ክንዋኔዎቻቸዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ግልፅነት መጉደልና ሙሉ አለመሆን ምክንያት የተለያየ አሰራር የነበረ ሲሆን በፍ/ቤቶችም ዘንድ አጨቃጫቂ ሆኖ ቆይቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት (የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት) ይህን ችግር ለማስቀረትና ወጥነት ያለዉ የሕግ አፈፃፀም እንዲኖር ለማስቻል በፍ/ቤት ቀጠሮ አሰጣጥ እና ክንዋኔዎቻቸዉ እንዲሁም ባልቀረቡ ተከራካሪዎች ላይ የሚያስከትለዉን ዉጤት በሚመለከት የሕግ ትርጓሜ ሰጥቶ እናገኛለን፡፡ በስር ፍ/ቤቶችም ዘንድ በአስገዳጅነት ተፈፃሚ እንዲሆን ያትታል፡፡[9] ሆኖም ግን ይህ ጉዳይ አሁንም በፍ/ቤቶቻችን ዘንድ በተለያየ ጊዜ ሲያከራክርና ወጥነት በጎደለሁ ሁኔታ ሲስተናገድ ይስተዋላል፡፡ በተከራካሪ ወገኖች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ ደግሞ ጉዳዩ ትኩረት እንዲሻ ያደርገዋል፡፡[10] በዚህ ጽሁፍ በፍትሐብሄር ችሎት የፍ/ቤት ቀጠሮ ትርጉም እና የሚተገበሩት የፍ/ቤት ክንዋኔዎች እንዲሁም ተከራካሪ ወገኖች የቀጠሮ ጊዜ አክብሮ አለመገኘታቸው የሚያስከትለውን ውጤት ግልፅ ማድረግ በዜጎች ላይ የሚደርሰዉን የመብት ጥሰትና እንግልት ለማስቀረት ያግዛል፡፡ ለዚህ ጽሁፍ ዝግጅት መጽሐፍትን፣ ሕጋጋትንና የፍ/ቤት ዉሳኔዎችን ጸሐፊዉ ዳስሷል፡፡ በመሆኑም በፍትሐ-ብሄር ችሎት ክርክር የፍ/ቤት ቀጠሮ ትርጉም፣ ዓላማ እና የተከራካሪ ወገኖች በቀጠሮ አለመቅረብ ከሚያስከትለው የሕግ ውጤት ጋር በማያያዝ በዚህ ጽሑፍ ለማካተት ተሞክሯል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጽሑፍ በቦታና የጊዜ

---

[8] ዝኒ ከማሁ 29-50.

[9] የፌዴራል ፍ/ቤቶችአዋጅ, ቁጥር 41234/2013 ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 2013 ቁጥር 26 (3).

[10] 'Apearance of Parties and Consquences of Non-Apearance' (28 August 2021) 1 <https://advocatespedia.com/APEARANCE_OF-PARTIES_AND_CONSQUENCES_OF_NON-APEARANCE> accessed on 25 August 2021.

እጥረት ምክንያት በአፈፃፀም ወቅት ስለሚነሱ ጉዳዮች አላካተተም። በመሆኑም አንባቢያን ይህን ታሳቢ እንዲያደርጉ ጸሐፊዉ ለማስታወስ ይወዳል።

## 2. የፍ/ቤት ቀጠሮ ትርጉም እና ዓላማቸው

የፍ/ቤት ቀጠሮ ማለት አንድን ክርክር ለማየት የተሰየመው ፍ/ቤት እንድን ጉዳይ በሕግ እና ማስረጃ መርምሮ ውሳኔ ለመወሰንና የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለመተግበር በችሎት ለተከራካሪዎች የሚይዘው ቀንና ሰዓት ማለት ነው።[11] የፍ/ቤት ቀጠሮ መሠረታዊ ዓላማ አንድን ክርክር በመመርመር ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊና (የተከራካሪዎችንና የፍ/ቤቱንም ወጪን የሚቀንስ) ቀልጣፋ ዉሳኔ ለመስጠት ነው።[12] የተቀላጠፈ እና ወጪን የሚቀንስ ፍትሕ መስጠት ለመቻል የክርክር ብዛትና ዉስብስብነት፣ የዳኞች ቁጥር መጠን፣ የፍ/ቤቶች ወይም የችሎት ብዛት፣ የዳኞችና የተከራካሪዎች የሕግ እዉቀት እና የጉዳይ ፍሰትን የማስተዳድር ብቃት ይወስኑታል።[13] የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከሚያዝዘዉ ዉጪ መተግበር ለፍትሕ መጓተት እና ለአላስፈላጊ ወጪ ይዳርጋል።[14]

ቀጠሮ በተለያየ ምክንያት ሊሰጥ ይችላል። ለምሳሌ፡ በዳኞች በራሳቸዉ አነሳሽነት (ሳይዘጋጁ በመምጣት ወይም ጉዳዩን በደንብ ባለመመርመር ምክንያት)፣ በተካራካሪዎች ወይም በምሥክሮች አነሳሽነት (በተሰጠዉ ቀጠሮ ከአቅማቸዉ በላይ በሆነ ምክንያት መገኘት

---

[11] 'Adjournments' (Center for Public legal Education Alberta, 2021) 1 <https://www.cplea.ca/wp-content/uploads/Adjournments.pdf> accessed on August 20, 2021; Munir Ahmad Mughal, 'Law As To Postpone Or Adjourn Criminal Proceedings' (29 July 2012)3 <https://papers.ssrn.com/sol3/papers.cfm?abstract_id=2119465> accsessed on 20 August 2021.

[12] አበበ 12; Sime 22, Para. 12.01 ; 'Adjournments and timely decision making' (National Domestic and Family Violence Bench Book) <https://dfvbenchbook.aija.org.au/fair-hearing-and-safety/adjournments-and-timely-decision-making/> accessed on 22 August 2021.

[13] Abrham Yohannes, 'The Purpose of Civil Procedure Vis-à-vis Fundamental Procedural Rules' (Ethiopian Legal Brief, 11 June 2021) <https://chilot.me/knowledge-base/the-purpose-of-civil-procedure-vis-a-vis-fundamental-procedural-rules/> accsessed on 20 August 2021.

[14] ዝኒ ከማሁ.

ባለመቻላቸዉ)፣ በጠበቆች አነሳሽነት (በችሎት መደራረብ፣ ባለመዘጋጀት ወይም በመቀያየር) ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡[15]

ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በአግባቡ ለመጨረስ እና ፍትሕን ለማስፈን የሚያስችለዉን ጊዜ ብቻ መጠቀም አለበት፡፡[16] በመሆኑም በዝግጅት ማነስ እና ሆን ተብሎ ጉዳዩን ለማጓተት በማሰብ ቀጠሮ መስጠት የለበትም፡፡[17] ፍ/ቤቱ አንድን ጉዳይ ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ቀጠሮ ማጠናቀቅ ካልቻለ ፍትሕን ያዘገያል፤ የዘገየ ፍትሕ ደግሞ እንደተነፈገ ይቆጠራል ('Justice delayed is justice denied') ከሚለዉ ብሂል ጋር ሲደመር በማሕበረሰቡ ዉስጥ ፍትሕን ለማስፈን አስቸጋሪ የሆነ ዉጤትን ያመጣል፡፡[18] ማሕበረሰቡ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ያለዉን አመኔታም ያሳጣል፤ እንዲሁም ለማህበራዊ ቀዉስ ይጋብዛል፡፡[19] ቀጠሮ ፍትሕን ከሚያጓትቱ ምክንያቶች አንዱ በመሆኑ ቀጠሮን መቀነስና አጭር ቀጠሮ መስጠት የተቀላጠፈ ፍትሕ እንዲኖር ያስችላል፡፡[20] ለሚከናወነዉ ተግባር ቀጠሮ መስጠትና የጊዜዉን እርዝማኔ በሕግ መደንገግ ፍ/ቤቶች በተወሰነ ጊዜ ብዙ ጉዳይ እንዲጨርሱ ያስችላል በተጨማሪም የዳኞችን

---

[15] Edward Laws, 'Addressing Case Delays Caused by Multiple Adjournments' (Gevernance, Social Development, Humanitarian Conflict (GSDRC), Helpdesk Research Report, June 2016) 1-2 <https://assets.publishing.service.gov.uk/media/57a9c983e5274a0f6c000006/HDQ1374.pdf> .accessed on 22 August 2021 [Here in after Edward]; World Bank, 'Uses and Users of Justice in Africa: The Case of Ethiopia's Federal Courts' (World Bank, 2010) 78 <https://openknowledge.worldbank.org/handle/10986/2937> accessed on 22 August 2021[Here after World Bank].

[16] Edward 7; Milosevic Fiske LLP, 'Considerations When Deciding on Motions for Adjournment' (9 May 2019). <https://www.mlflitgation.com/media/considerations-when-deciding-on-motions-for-adjournment/> accessed on 25 August 2021.

[17] Stuart Rabner and Hon. Glenn A. Grant, 'A Practitioner's Guide to New Jersey's Civil Court Procedures' (New Jersy Courts, 2011) 15-2 <https://www.njcourts.gov/attorneys/assets/appellate/practitionersguide.pdf> accessed on 22 August 2021 [Here after Rabner and Grant].

[18] Edward 2.

[19] ዝኒ ከማሁ.

[20] World Bank 75-79, 83.

የአፈፃፀም ብቃት ለመገምገም እና በተግባር የቀጠሮ ብዛትና የጊዜ መራዘምን ለማስቀረት ከሚቻልባቸዉ አማራጮች አንዱ ነዉ፡፡[21]

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 192-199 ስለ ቀጠሮና የጊዜ አወሳሰን በሚመለከት ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በሕጉ ቁጥር 192 አንድን ክርክር ለማከናወን መደረግ ወይም መፈጸም የሚገባዉ ነገር ሲኖርና የሚፈጸምበት ጊዜ በሕግ ተወስኖ ካልተገኘ ፍ/ቤቱ የነገሩን አካባቢ ሁኔታ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ሊወስን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡[22] በሕጉ የተቀመጠ ጊዜ ሲኖር ግን በተለየ ሁኔታ ካልተፈቀደ በቀር ፍ/ቤቱ ይህንን ጊዜ ማሳጠርም ሆነ ማስረዘም እንደማይችል ያስገነዝባል፡፡[23] እንግዲህ የጊዜ ስሌቱ እንዴት ይሰላ ለሚለዉም በፍትሐ-ብሄር ሕግ ቁጥር 1848 መሠረት መሆን እንደሚገባ በግልጽ ተቀምጧል፡፡[24] የፍትሐ-ብሄር ሕግ ቁጥር 1848 በሕጉ አደረጃጀት ስለዉል በጠቅላላዉ ከሚደነግገዉ ክፍል ዉስጥ የሚገኝ ሲሆን ስለጊዜ አቆጣጠር ይደነግጋል ይህንንም አሁን ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር አጣምረን ማየት ይኖርብናል፡፡ ቁጥር 1848 ስለዉል በጠቅላላዉ በሚዘረዝረዉ በሕጉ አራተኛ መጽሐፍ ምዕራፍ ሦሥት ክፍል ሥድስት የሚገኝ ይዘቱም የዉል መብትና ግዴታ በይርጋ ጊዜ ስለሚቋረጥበት አግባብ በሕጉ የተደነገገ በመሆኑ ይህን የይርጋ ጊዜ የአቆጣጠር ስሌት መደንገግ ያለመ ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት የቀጠሮ ጊዜ ስሌት የመጀመሪያዉን ቀን እንደማያካትት እና የሚያበቃዉም ለቀጠሮዉ የተወሰነዉ ጊዜ የመጨረሻዉ ቀን ካለፈ ነዉ፡፡[25] የቀጠሮዉ የመጨረሻ ቀን ምናልባትም ቀጠሮዉን በሠጠዉ ፍ/ቤት በሚገኝበት ቦታ በሕግ የሚታወቅ የበዓል ቀን የሆነ እንደሆነ የቀጠሮ ጊዜዉ የሚያበቃዉ ከበዓሉ ተከታይ በሆነዉ የስራ ቀን እንደሆነ

---

[21] ዝኒ ከማሁ; Edward 9-10; ሚስ አኒ-ሊሴ ሲቦኒ, 'የፍትሕ ሥርዓቶች የሥራ አፈፃፀም ጥራትና ዉጤት ግምገማና አለካክ' (ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ የተካሄደ ሪፖርት በአቅም ግንባታ ሚኒስተር'የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም, 1994) 69-70.

[22] የኢትዮጲያ ፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ, ነጋሪት ጋዜጣ 1957 ቁጥር192 (1). [ከዚህ በኋላ የፍ/ብሥ/ሥ/ሕግ ተብሎ ተጠቅሷል]፡፡

[23] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 192(2).

[24] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 192(3).

[25] የኢትዮጵያ ፍትሐብሄር ሕግ አዋጅ ቁጥር 2/1952 ነጋሪት ጋዜጣ (1952) ቁጥር 1848(1-2).

ያስገነዝባል።[26] በዚህም መሠረት የቀጠሮ ጊዜ ተከበረ የሚባለዉ እንዲከወን የተሰጠዉ ተግባር ቀኑ ከማብቃቱ በፊት ከተፈፀመ ብቻ ነዉ።[27]

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን ያለበት ድርጊት በተወሰነዉ ጊዜ ውስጥ ካልተከናወነ ዋጋ ቢስ ነዉ። ምክንያቱም ሕጉ *"አንድ ነገር እንዲፈፀም ከተወሰነዉ ጊዜ በኋላ ቢፈፀምም እንዳልተፈፀመ ሆኖ ይቆጠራል"* በማለት ይደነግጋል።[28] የዚህ ድንጋጌ ዓላማ የተቀላጠፈ ፍትህ እንዲኖር ማስቻል አንዱ ነዉ። ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የማይሆነዉ በፍ/ቤት ዉሳኔ መሠረት ተለዋጭ ቀጠሮ ሲሰጥ ብቻ ነዉ። ተለዋጭ ቀጠሮ የሚሰጠዉ በቀጠሮዉ ቀን እንዲፈፅም የታዘዘ ሰዉ ወይም ባለጉዳይ መፈፀም ያልቻለዉ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነና መሰናክሉ ከተወገደ በአስራ አምስት ቀን ዉስጥ ጉዳዩን ለሚከታተለዉ ፍ/ቤት ተለዋጭ የጊዜ ቀጠሮ እንዲሰጠዉ ሲያመለክትና ፍ/ቤቱም ምክንያቱን ሲቀበለዉ ነዉ።[29] ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሚያስብሉት ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ሕጉ አላብራራም። ይልቁንም ሕጉ የመረጠዉ ከአቅም በላይ ተብሎ የማይቆጠሩትን ሁኔታዎች መዘርዘር ነዉ። በዚህም መሠረት በሥራ ብዛት፣ በመዘንጋት፣ በቸልተኝነትና በራሱ ጉድለት መሆኑ በታወቀ ጊዜ እንደ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት እንደማይቆጠርና አዲስ የጊዜ መራዘም ዉሳኔ እንደማይሰጠዉ ሕጉ ያስገነዝባል*።[30]*

በራሱ ጉድለት የሚባለዉ ባለጉዳዩ ሆን ብሎ ጉዳዩን ለማጓተት ወይም በቸልተኝነት ሳይቀርብ ወይም የታዘዘዉን ሳይፈፅም ሲቀር ነዉ።[31] በቂ ተብሎ የሚገመት ምክንያት እንደነገሩ ሁኔታ የሚታይ ሲሆን ከግምት ዉስጥ መግባት ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ፡ ቀጠሮ ያላከበረዉ ባለጉዳይ ከመዘግየቱ ተጠቃሚ የማያደርግ ወይም አክብሮ የተገኘዉን

---

[26] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 1848(3).
[27] የፍ/ብሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 193.
[28] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 195.
[29] ዝኒ ከማሁ ቁጥር196.
[30] ዝኒ ከማሁ ቁጥር196(3).
[31] Narayan Subramanian, Sufficient Cause (Apr 20, 2015) 2 <https://www.scribd.com/document/262469686/Sufficient-Cause> accessed on August 22 2021.

ተከራካሪ የማይጎዳ፣ ባለጉዳዩ ባይሰማ ፍትሕ የሚያዛባ (ዉሳኔዉን የሚለዉጥ ሲሆን) ፣ ባለጉዳዩ ሆን ብሎ ክርክሩን ለማዘግየት ወይም በቸልተኝነት ያልቀረ መሆኑን ከግምት ዉሥጥ መግባት አለበት።[32] በቂ ምክንያት ነዉ ለማለት ከተሟጋቹ ቁጥጥር ዉጪ ነዉ በሚያስብል (በተፈጥሮ ወይም ሰዉ ሰራሽ አደጋ) ምክንያት መሆን አለበት።[33] "An avoidable cause for delay by due care and attention cannot be sufficient cause. Cause attributable to negligence or inaction of the party cannot be sufficient cause."[34] ለምሳሌ፡ የትራንስፖርት መዘግየት ባለጉዳዩ ጥፋት ከሌለበት እንደበቂ ምክንያት ሊቆጠር ይችላል፤ የጸጥታ ችግር (ብጥብጥ) ምክንያት እንዲሁም የቀጠሮዉን ቀን መሳሳት ጉዳዩን ለማዘግየት አስቦ ካልሆነ በቂ ምክንያት ሊባል ይችላል።[35] ጥፋት የሌለበት (ታማኝ) ባለጉዳይ ጠበቃዉ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ባለመቅረቡ ምክንያት ፍትሕ ሊነፈገዉ ስለማይገባ በባለጉዳዩ ጉድለት ነዉ መባል የለበትም የሚል አተያይም አለ።[36] ምክንያቱም በፍትሕ ስርዓቱ መተማመን ትልቅ ቦታ ያለዉ በመሆኑ አንድ ባለጉዳይ በትጋት ጠበቃዉን መከታተል የግድ የሚባል አይደለም በሚል ነዉ።[37] ሥለሆነም ፍ/ቤቱ በቂ ምክንያት ነዉ አይደለም የሚለዉን ለመወሰን የቀጠሮዉ መራዘም ባልቀረበዉ ተከራካሪ ላይ እንዲሁም የተቀላጠፈ ፍትሕ ለማስፈን የሚያሳድረዉን ተጽዕኖ ከግምት ማስገባት አለበት።

አንድን የፍትሐ-ብሄር ጉዳይ ለማየት የተሰየመ ፍ/ቤት የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለመፈጸም እና ጉዳዩን ዐይቶ ለመወሰን በርካታ እና የተለያዩ ቀጠሮዎች እንደሚሰጥ ይታወቃል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 197 መሠረት ክርክሩ በሚሰማበት በማናቸዉም ጊዜ ፍ/ቤቱ ተገቢ መስሎ ሲታየዉ ወይም በቂ ምክንያት ሲያገኝ ለተከራካሪዎች ወይም ለአንደኛዉ ወገን ነገሩ

---

[32] ዝኒ ከማሁ

[33] Abhavya Rabra, 'Appearance and Non-Appearance of the Parties' (2018) Vol 4 Journal on Contemporary Issues of Law 328 <https://jcil.lsyndicate.com/wp-content/uploads/2018/09/37.-Abhavya.pdf> accessed on 24 August 2021.

[34] ዝኒ ከማሁ n 34.

[35] ዝኒ ከማሁ.

[36] ዝኒ ከማሁ n 36.

[37] ዝኒ ከማሁ

የሚሰማበትን ቀን በመወሰን ጊዜ ይሰጣል፡፡[38] የሚሰጠዉም ጊዜ ለቀጠሮዉ ምክንያት የሆነዉን ጉዳይ ለማከናወን በቂ ሆኖ የሚገመተዉ ጊዜ ብቻ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በቂ ምክንያት እንደ ጉዳዩ አካባቢያዊ ሁኔታ የሚወሰን ሲሆን ይህም ድንጋጌ ፍ/ቤቶች የሚሰጡት የጊዜ ቀጠሮ ፍትህን ለማዓተትና ባለጉዳዮችን ለማጉላላት ባለመ መልኩ መሆን እንደሌለበት ያስገነዝባል፡፡[39] ፍ/ቤቱ ቀጠሮ በሚሰጥበት ጊዜ ለቀጠሮዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ በሚገባ እንዲከናዎን አስፈላጊዉን ትዕዛዝ መስጠትም ይኖርበታል::[40] በመሆኑም በፍ/ቤት የሚሰጠው ቀጠሮ በቀጠሮው ቀንና ሰዓት የሚተገበረውን ክንዋኔ ለመተግበር የሚመለከታቸው አካላት ማለትም መዝገብ ቤት፣ ሬጅስትራር፣ ዳኞች፣ ተከራካሪ ወገኖች፣ የሰው ምስክሮች፣ እንዲሁም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለተያዘው ጉዳይ ሙያዊ ምስክርነት እንዲሰጡ እንደነገሩ ሁኔታ የሚታዘዙ አካላት/ሰዎች/ እንደ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ጊዜውን ጠብቀው ተገቢዉን ክንዋኔ እንዲፈፅሙ ያስችላል፤ መፈፀምም ይኖርባቸዋል፡፡ በተለየ ሁኔታ ባለጉዳዮች በቀጠሮ ቀን ካልቀረቡ መብታቸዉን የሚጎዳ ዉጤት ስለሚኖረዉ ይህን በሚገባ ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡[41]

## 3. በፍትሐብሔር ክርክር የፍ/ቤት ቀጠሮ፣ የሚከናወኑ ተግባራትና በቀጠሮ ቀን የተከራካሪ ወገኖች ፍ/ቤት አለመቅረብ የሚያስከትለው ውጤት

አንድን ጉዳይ ለማየት የተሰየመ ፍ/ቤት የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለመፈጸም እና አንድን ጉዳይ አይቶ ውሳኔ ለመወሰን በርካታ ቀጠሮዎችን ሊሰጥ ይችላል፡፡ ከሚሰጣቸዉ ቀጠሮዎች ዉስጥ የተከሳሽን መልስ ለመቀበል፣ ክስ ለመስማበት፣ ማስረጃ ለመስማትና ምስክሮችን ለመመርመር፣ መዝገቡን መርምሮ ተገቢውን ትዕዛዝ ለመስጠት፣ በሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ የሌላኛውን ወገን አስተያየት መቅረብ ለመጠባበቅ፣ ማስረጃ እንዲቀርብ ለመጠባበቅ፣ መርምሮ ውሳኔ ወይም ፍርድ ለመስጠት የሚሰጥ የቀጠሮ ቀንን ያጠቃልላል፡፡ ይህም

---

[38] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 197.

[39] ዝኒ ከማሁ. See also, [Narayan Subramanian](), Sufficient Cause (20 April 2015) <https://www.scribd.com/document/262469686/Sufficient-Cause> accessed on 22 August 2021.

[40] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 198(1).

[41] ዝኒ ከማሁ n36.

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 127-131፣ 241፣ 258፣ 145፣ 249፣ 180፣ 181 እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት ስር ተደንግጎና ትርጉም ተሰጥቶበት ይገኛል። የኢትዮጵያ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ የተከራካሪ ወገኖች በቀጠሮ አለመቅረብ እና የሚያስከትለዉን ዉጤት ለመወሰን ከሚጠቀምባቸዉ መስፈርቶች ተከራካሪዉ በቀረበት ቀጠሮ ፍ/ቤቱ ሊከዉን የሚገባዉን ጉዳይ አንዱ ስለሆነ[42] በፍትሐብሄር ክርክር ፍ/ቤት ስለሚሰጠዉ ቀጠሮና ክንዋኔ ማብራራቱ ተቀዳሚ ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ክፍል ተብራርቷል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳዉ ጉዳይ ከተከራካሪ ወገኖች የአንዱ ወይም የሁለቱም ፍ/ቤት በያዘው ቀነ-ቀጠሮ አለመገኘት የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ነጥብም በዚህ ክፍል ተዳሷል።

የተከራካሪ ወገኖች ለችሎት የሚቀርቡበትን ሂደት በሚመለከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(1) መሠረት ነገሩን ለማየት ፍ/ቤቱ በሰጠው ቀጠሮ ከሳሽ እና ተከሳሽ ራሳቸው ወይም በወኪሎቻቸው ተሟልተው መቅረብ እንዳለባቸው በግልፅ ሰፍሯል። ዉክልናዉ ዉጤታማ እንዲሆን በጽሑፍና ወካዩ ሊፈርምበት ይገባል።[43] ስለሆነም ተከራካሪ ወገኖች በወኪሎቻቸው ወይም አስፈላጊ በሆነ ሰዓት እራሳቸው የፍ/ቤት ቀጠሮውን አክብረው፣ እንዲያከናውኑ የታዘዙትንም ፈፅመዉ ለችሎት መቅረብ ተገቢ ነዉ።[44] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ዓላማ የፍትሐ-ብሄር ጉዳዮችን ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ ዉሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ በመሆኑ የተከራካሪዎች በችሎት መገኘትን በሚመለከት በተከራካሪዎቹ ላይ ብሎም በፍ/ቤት የሚደርሰዉን ችግር ለመግታት ጠንከር ያለ አቋም አለዉ።[45]

---

[42] Balew Mersha and Mizane Abate, *Ethiopian Civil Procedure Notes, Cases and Questions, (*Bahir Dar and Jimma universities, 2010) 217, Para.3. [Here after Balew and Mizane].

[43] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 66(2).

[44] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 65(1) ፣ 66፣ 75(1) ፣ 77፣ 338(1) cum 339 (3).

[45] አበበ 12; Sedler 161-162.

*"An appearance involves coming before the court so that the court can adjudicate the case or take any other action it deems necessary. While a personal appearance is not ordinarily required, the court has the power to compel personal attendance of parties where the court concludes such attendance is necessary for the determination of the question in the suit, and if a party who has been ordered to appear fails without good cause, it is considered as if there was no appearance.*

ዘመናዊ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተከራካሪዎች ተገደዉ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ባይሻም ተከራካሪዎች መጥሪያ ደርሷቸዉ ካልቀረቡና ካልተከራከሩ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በሌሉበት በማየት እነሱን የሚጎዳ ዉሳኔም ሊወስን ይችላል።[46] ፍ/ቤት ያልቀረበዉ ተከራካሪ እስኪቀርብ ድረስ ምንም ሳያደርግ የሚጠብቅ ከሆነ ፍትህ እንዲዘገይ፤ ቀጠሮዉን አክብሮ የሚገኘዉ ተካራካሪ ጥቅም እንዲጎዳ ያደርጋል።[47] ይህ እንዳይሆን እንዲሁም በፍ/ቤት ደጋግሞ ቀጠሮ መስጠቱ የሚያስከትለዉን መጨናነቅ (case load) ለመቀነስ ሲባል ሕጉ የተከራካሪዎች በፍ/ቤት አለመገኘትና የሚያስከትለዉን ዉጤት በጥብቅ መደንገጉ አስፈላጊ ነዉ።

ፍ/ቤቱ የጉዳዩን ሂደት ለመቆጣጠር፣ የሚሰጠዉ ትዕዛዝ እንዲፈፀም እና በክርክር ሂደቱ ላይ ሙሉ ቁጥጥር እንዲኖረዉ አግባብነት ያለዉ የማስገደድ ሀይል ሊኖረዉ ያስፈልጋል።[48] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት ፍ/ቤት በቀጠሮ ቀን አለመቅረብ ከሚስከትላቸዉ ዉጤቶች መካከል መዝገብ መዝጋት፣ ክስ መዝጋት፣ በጽሑፍ የመከራከር መብት መታለፍ፣ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት እና የቀረዉ ወገን በሌለበት የክሱ ጉዳዩ መሰማት መቀጠል ናቸዉ። የባለጉዳዮች ወደ ፍ/ቤት መቅረብና አለመቅረብ የሚያስከትለውን ውጤት ምን እንደሆነ በሕጉ ከቁጥር 65 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመላክቷል።

እስካሁን የተሰጠዉን መንደርደሪያ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት አራት ንዑስ ከፍሎች በፍትሐ-ብሄር ክርክር ፍ/ቤት ስለሚሰጣቸዉ ቀጠሮዎችና በእያንዳንዱ ቀጠሮ ስለሚተገብረዉ ክንዋኔ እንዲሁም ከተከራካሪዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱም በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ ስለሚያስከትለዉ ዉጤት ተብራርቷል።

---

*The code is strict on the requirement of appearance."* It aimed to avoid delay and occurance lots of problems both to the parties and to the court.

[46] *American Jurisprudence* (2nd ed., Vols. 16A, 26 & 59, the Lawyer Cooperative Publishing Co., 1972) 1033.

[47] ዝኒ ከማሁ.

[48] Sime 351.

### 3.1. የተከሳሽን መልስ ለመቀበል በተሰጠ ቀጠሮ ቀን

በዚህ ንዑስ ክፍል የተከሳሽን መልስ ለመቀበል በተሰጠ ቀጠሮ የፍ/ቤቱን ክንዋኔ እና ከተከራካሪዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ቢቀሩ ስለሚከተለዉ እርምጃ ተብራርቷል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ክርክሩ ፈር የሚይዘዉ በጽሑፍ ክርክር ሲሆን ፍ/ቤት ለዉሳኔዉ ጭብጥ ለመያዝ፣ ክሱ መሰማት በሚጀምርበት ጊዜ ግራቀኙ የሚሰጡት ምላሽ ፍ/ቤቱ የጽሑፍ ክርክርሩ ላይ ተመሥርቶ በሚያቀርብላቸዉ ጥያቄ በመሆኑ በፍርድ ሂደቱ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡[49] መልስ ለመቀበል ቀጠሮ የሚያዘው በአንድ ጉዳይ ክስ የተመሰረተበት ሰው በጉዳዩ ላይ የቀረበበትን ክስ ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ ክርክሩን ወይም መልሱን በጽሑፍ እንዲያቀርብ ማስረጃም ካለው የማስረጃውን ዝርዝር እና ማስረጃዎችን ለፍ/ቤቱ በማቅረብ የጽሑፍ ክርክሩን እንዲያሟላ ለማድረግ ነው፡፡[50] በዚህ ቀጠሮ ተከሳሽ የጽሑፍ መልሱን ይዞ ከቀረበ ፍ/ቤቱ የጽሑፍ መልሱን ከማህደሩ ጋር በማያያዝ ጉዳዩን ለተከታዩ ክንውን ማለትም ለክስ መስማት ይቀጥራል፡፡[51] በዚህ ቀጠሮ በልዩ ሁኔታ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር ከከሳሽ በኩል መልስ ከመቀበል በተጨማረነት የሚከወን ተግባር የለም፡፡[52] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223(2) እና 234 መሠረት የክሱ ማመልከቻና ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡት የጽሑፍና ሌሎች ማስረጃዎች እንዲሁም የምስክሮች ዝርዝርና ማንኛውም ለፍ/ቤቱ የደረሱትን መግለጫዎች ትክክለኛ ግልባጮች ለተከሳሹ ሊደርሰው እንደሚገባ ሁሉ ተከሳሹም የሚያቀርበው መልስና የመከላከያ ማስረጃ (የሰነድ ወይም የምስክሮች ዝርዝር) ለከሳሽ ሊደርሰው እና ሊከራከርበት ይገባል፡፡[53] በመሆኑም የጽሑፍ መልስ ለመቀበል

---

[49] በታምራት ኪዳነማርያም, 'በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ጉዳዮች የቅድመ ችሎት ሙግት ሥርዓት (ክስ መስማት፣ ጭብጥ መያዝ)' (የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረታዊ ችግሮችና ማሻሻያዎቹ ላይ ያተኮረ ኮንፈረንስ, ዓለማየሁ ሃይሌ መታሰቢያ ድርጅት, 1998 ዓ.ም) 79-80 [ከዚህ በኃላ በታምራት ኪዳነማርያም ተብሏል፡፡›.

[50] ዝኒ ከማሁ;. see also የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 80-93, 182(2), 222, 241, 248, 233.

[51] መንበረፀሃይ ታደሰ, *የኢትዮጲያ ሕግና የፍትህ ገፅታዎች (*አዲስአበባ 1999) 78 [ከዚህ በኃላ መንበረፀሃይ ተብሏል]; Sedler 161.

[52] ዝኒ ከማሁ.

[53] እነ ፕሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት *v* አቶ ልመንህ ተፈራ [2002] 9-የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት መ/ቁ 45984, 290.

በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ ምናልባት ተከሳሽ ባይቀርብ መጥሪያ በአግባቡ ማድረሱን ከማያሳዉቅ በቀር እንዲፈጽም የሚጠበቅበት ተግባር የለም፡፡

በአንፃሩ ክስ ለመስማት በተሰጠ ቀጠሮ ፍ/ቤቱ ብዙ ክንዋኔዎችን የሚፈፅምበት (በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 248 (ሐ) መሠረት ጭብጥ መመሥረት፣ በሕጉ 242 መሠረት በታመነዉ መጠን ሙግቱን መግታት ወይም በከፊል ዉሣኔ መሥጠት፣ ተከሳሹ በክሱ ላይ የተዘረዘረዉን እና በመልሱ ላይ በቀጥታ ወይም እንደ ነገሩ አካባቢያዊ ሁኔታ እንደተካደ የሚቆጠረዉን ነገር የሚያምን ወይም የሚክድ መሆኑን የሚጠይቅበት) ፣ አንዱ ወገን ስለባላጋራዉ ክርክር ግልጽ ያልሆነ ካለ እንዲብራራለት ጥያቄ የሚጠይቅበት በመሆኑ ከከሳሹም ሆነ ከተከሳሹ ብዙ ይጠበቃል፡፡[54] ክስ ለመስማት ስለሚሰጥ ቀጠሮ ከታች በንዑስ ክፍል 2.2 ስለተብራራ አሁን የዚህ ክፍል ርዕሰ ጉዳይ ወደሆነዉ ሌላዉ ጉዳይ እንመለስ፡፡

ይህም ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱ መልስ ለመቀበል በተሰጠ ቀጠሮ ዕለት ባይቀርቡ ስለሚከተለዉ ዉጤት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 233 መሠረት ተቀባይነት ያገኘ ክስ ከተመሠረተ ፍ/ቤቱ ክሱን ተቀብሎ የቀረበለትን ክስ፣ ማናቸውም አስረጅና የጽሑፍ ግልባጭ ከመጥሪያው ጋር ለተከሳሽ እንዲደርሰውና ተከሳሽም የመከላከያ መልሱን በጽሑፍ እንዲያቀርብ ቀጠሮ ይሰጣል፡፡ ካልቀረበ ግን ጉዳዩ በሌለበት እንደሚሰማ (default in pleading) ይገለፅለታል ይላል፡፡ የዚህን ቀጠሮ ክንዉን እንዲሁም ፍ/ቤት ባልቀረቡት ወገኖች ላይ ስለሚከተለዉ ዉጤት የሚደነግገዉ ይህ አንቀጽ ሲሆን የአማርኛና የእንግሊዘኛ ቅጂዉ መለያየት በጉዳዩ ላይ ብዥታ እንዲኖር አድርጓል፡፡ መልስ ለመቀበል በሚሰጥ ቀጠሮ ላይ የፍ/ቤቱ ክንዉን ምን እንደሆነና የተከራካሪዎች አለመቅረብ የሚያስከትለዉን ዉጤት አስመልክቶ ሕጉ ግልፅነት የጎደለዉ ወይም የሚለዉ ነገር የሌለዉ መሆኑ ሌላዉ ምክንያት ነዉ፡፡ ይህ ጉዳይ በተግባር የበለጠ መወሳሰብን ፈጥሯል፡፡ ለምሳሌ *በሼል ኢትዮጵያ አ/ማ እና*

---

[54] መንበረፀሃይ 78; በታምራት ኪዳነማርያም 80-81.

*በወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ*[55] መካከል በነበረዉ ክርክር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሹ መልስ በተቀጠረበት ቀን የክስ መልሱን አዘጋጅቶ ፍ/ቤት ማቅረብ ባለመቻሉ ይህን ቀጠሮ ክስ ለመስማት እንደተቀጠረ በመቁጠር ክስ መስማተን የሚመለከቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ተግባራዊ በማድረግ ተከሳሽ በሌለበት ክስ እንዲሰማ ወስኗል፡፡ እንዲሁም *በአቶ ውርጌሳ ታደሰ እና አቶ መለሰ ተካ*[56] መካከል በነበረዉ ክርክር መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀጠሮ ከሳሽ ባለመቅረቡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መዝገቡን ዘግቶ አሰናብቷል፡፡ በእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች የተግባር ችግር የተፈጠረዉ የሕጉ መልስ ለመቀበል በሚሰጥ ቀጠሮ ላይ የፍ/ቤቱ ክንዉን ምን እንደሆነ ግልፅነት የጎደለዉ በመሆኑ ነዉ፡፡

በመሆኑም ተከሳሽ በዚህ ቀጠሮ ባይቀርብ ዉጤቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለዉን ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 233 መሠረት ተከሳሽ የክስ መልስ ይዞ እንዲቀርብ ያዛል፤ ካልቀረበ ወይም መከላከያ መልሱን ሳይዝ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ በሌለበት እንደሚሰማ መጥሪያዉ ላይ እንደሚገለፅለት ይደነግጋል፡፡[57] የዚህ ድንጋጌ የአማረኛና እንግሊዘኛ ቅጂ የተለያየ አንድምታ አለዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 233 የአማርኛ ቅጂ ከሕጉ ቁጥር 70(ሀ) በሚመሳሰል ሁኔታ ተከሳሽ በዚህ ቀጠሮ የጽሑፍ መልስ ይዞ ሳይቀርብና ክስ በሚሰማበት ቀጠሮ ሲቀር የሚወሰደዉ እርምጃ እኩል ሆኖ የጉዳዩ መሰማት በሌለበት (ex-parte proceeding) መቀጠል የሚመስል መሆኑ ነዉ፡፡ ይህ ድንጋጌ በከፊል "(...) ተከሳሹ መከላከያዉን ለፍ/ቤቱ ሳያቀርብ የቀረ ወይም እራሱ መከላከያ ሳይዝ የቀረበ እንደሆነ *ክርክር በሌለበት* የሚታይ መሆኑ በመጥሪያዉ ላይ ይገለፅለታል" ይላል፡፡[58] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 233 የእንግሊዘኛዉ ቅጂ በሌላ በኩል ተከሳሽ በዚህ ቀጠሮ መልሱን ይዞ ባይቀርብ የክስ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፎበት ክርክሩ እንደሚቀጥል ማለትም ቀጣዩ

[55] [1997] 1-3 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 60 (ከዚህ በኃላ ሼል የኢትዮጵያ አ/ማ *v* በወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ ተብሏል).

[56] [1997 ዓ.ም] 1-3 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 47 (ከዚህ በኃላ አቶ ውርጌሳ ታደሰ *v* አቶ መለሰ ተካ ተብሏል).

[57] ሼል የኢትዮጵያ አ/ማ *v* በወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ.

[58] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 233.

የፍ/ቤት ሥነ-ሥርዓት (የክስ መሰማት) ሂደት እንደሚቀጥል ያለመ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በሕግ አተረጓጎም ሂደት የአማርኛና እንግሊዘኛ ቅጂ መካከል ልዩነት ሲፈጠር የአማርኛ ቅጂ ሊተገበር እንደሚገባ የሚታወስ ነዉ፡፡[59] ይህ ደግሞ ጉዳዩን ይበልጥ ያወሳስበዋል፡፡

ሆኖም ግን የሕጉን መንፈስ ስንመረምርና የፌ/ጠ/ፍ/ሰ/ሰ/ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመመልከት መልስ ለመቀበል በተሰጠ ቀጠሮ የፍ/ቤቱ ዋና ክንዋኔ የተከሳሽን መልስ መቀበልና ከሳሽ ከቀረበ የተከሳሽን የጽሑፍ መልስ ለከሳሽ መስጠት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ቀጥሎምክስ የሚሰማበትን ቀን ለተካራካሪዎች ማሳወቅ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ በዚህ ቀጠሮ ፍ/ቤት ባይቀርብ የክስ መልስ የማቅረብ መብቱ ብቻ ታልፎ (default proceeding or default in pleading) የክስ ሂደቱ እንደሚቀጥል እንገነዘባለን፡፡ ለዚህም አንደኛዉ ማሳያ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የክስና መልስ ዝግጅትና የክስ መስማት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በተለያየ የሕጉ ክፍል መደንገጉ ነዉ፡፡ ከሕጉ አደረጃጀትም መገንዘብ እንደሚቻለው የክስና የመከላከያ ጽሑፎች (ከቁጥር 222-240 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት) ልውውጥ ከተከናወነ በኋላ ነው ክሱ የሚሰማው (241-273 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት)፡፡ [60] ሁለተኛዉ ማሳያ ደግሞ የሕጉን መንፈስ (notion of the law) መሠረት አድርጎና ወጥነት (consistencey) ባለዉ መልኩ በመተርጎም ነዉ፡፡ ለምሳሌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78 ላይ በአማርኛዉም ሆነ በእንግሊዘኛዉ ቅጂ በተመሳሳይ ሁኔታ ‘ተከሳሽ በጉዳዩ ላይ ክስ በሚሰጥበት ቀን ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ’ (ex-parte) ወይም ‘ተገቢዉን መከራከሪያ ሳይቀርብ’ (default in pleading) በማለት ያስቀመጠ በመሆኑ ሁለቱ ክንዋኔዎች የተለያዩ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ መልስ ለመቀበል በተሰጠ ቀጠሮ ቢቀር መልስ በጽሑፍ

---

[59] የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 3/1995, ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 1995 ቁጥር 2(4).
[60] የጽሑፉን ልውውጥ የሚመለከተው የሕጉ ክፍል "ስለክስና ስለመከላከያ ጽሁፍ" በሚል ርዕስ ራሱን የቻለ አንድ ክፍል ሲሆን በዚህ የጽሁፍ ልውውጥ በኋላ የሚከተለው ክንውን ደግሞ "ክስን ስለመስማት" በሚል ርዕስ ራሱን በቻለ በሌላ ምዕራፍ የምናገኘው ነው፡፡

የማቅረብ መብቱ ብቻ ከሚታለፍበት በቀር በሌለበት ክሱ ይታይ መባሉ የሕጉን መንፈስና ወጥነት የሚጎዳ ነዉ፡፡

በሼል ኢትዮጵያ አ/ማ ፟ና በወ/ሮ አስቴር ብርሃነስላሴ መካከል በነበረዉ ክርክር የፌ/ጠ/ፍ/ሰ/ሰ/ችሎት በሕጉ ቁጥር 70 (ሀ) እና 233 መካከል ያለዉን ብዥታ ለማስወገድ እንደሚከተለዉ አብራርቷል:

> *የጽሁፍ መልሱን ሳያቀርብ የቀረ ተከሣሽ በ233 መሠረት በሌለበት ጉዳዩ እንደሚሰማ ጉዳዩ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ ተከሣሽም በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳዩ በሌለበት እንደሚሰማ በቁጥር 70(ሀ) መሠረት ትዕዛዝ የሚሰጥበት ይመስላል፡፡ የሁለቱም ድንጋጌዎች የአማርኛ ቅጂ ለመልስ በተቀጠረበት ቀን መቅረትና ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን መቅረት አንድ አይነት ውጤት ያላቸው እንደሆነ የሚገልጹ ቢሆኑም የሁለቱም የእንግሊዝኛ ቅጂዎች ግን የተለየ ጽንሰ ሃሳብ የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡ የእንግሊዝኛ የ70 (ሀ) የእንግሊዝኛ ድንጋጌ ስለ Ex-parte ሲናገር የ233 ግን የሚደነግገው ስለ default proceeding ነው፡፡ ሁለቱም የተለያየ ይዘት የተለያየ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡*[61]

ይህ የሚያሳየዉ በሁለቱ ቀጠሮዎች ፍ/ቤቱ የተለያየ ክንዉን ነዉ መተግበር ያለበት፡፡ መልስ ለመቀበል በተሰጠ የቀጠሮ ዕለት ፍ/ቤት ክሱን የሚሰማበት አይደለም፡፡ በመሆኑም ከሣሹ በዚህ ቀጠሮ ባይቀርብ እንዲፈጽመው የታዘዘው ነገር ስለሌለ ፍ/ቤቱ ቀጣዩን ክንውን አስመልክቶ ትዕዛዝ የሚሰጥ ሲሆን የከሣሹን መዝገብ መዝጋት አይገባም፡፡ ከላይ እንደተብራራዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የተከራካሪዎች አለመገኘትና ዉጤቱን በሚመለከት ሲደነግግ መሠረት ካደረጋቸዉ ውስጥ አንዱ በቀጠሮዉ ዕለት የፍ/ቤቱ ክንዉን ወይም ተግባር ነዉ፡፡ በሁለቱም ቀጠሮዎች የተከሳሽ አለመቅረብ ዉጤቱ ተመሳሳይ ነዉ ማለቱ ከአመክንዮ የራቀ ነዉ፡፡ አንድ ሰዉ የጽሑፍ መልስ ካላቀረበ አግባብነት የሚኖረዉ የ default proceeding መሠረተ-ሃሳብ ሲሆን ይህም “አንድ ተሟጋች እንዲፈፅም የታዘዘዉን ነገር

---

[61] ሼል የኢትዮጵያ አ/ማ *v* በወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ 63.

ሳያሟላ ቢቀር ዕድሉ እንዳመለጠዉ የሚቆጠር ነዉ።"[62] "ከክርክር እንዲወጣ ግን አይደረግም።"[63] "A default judgment can be obtained against a party who has failed to respond, *i.e.*, "plead" (…)::"[64] በዚህ ቀጠሮ የፍ/ቤቱ ክንዋኔ የተከሳሽን የጽሑፍ መልስ መቀበል እና ለሌላኛዉ ተከራካሪ ወገን መስጠት ነው።

ሥለሆነም ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ያልቀረበው መጥሪያ በአግባቡ ደርሶት በቂ ባልሆነ ጉድለት መሆኑን ከተረዳ ተከሳሽ በጽሑፍ መልስ የማቅረብ መብት እና ክርክርን በጽሑፍ ከማቅረብ ጋር ተያይዘዉ የሚመጡ ጥቅሞች ወይም መብቶች ይታለፉበታል። ከጽሑፍ መልስ ጋር ተያይዘው ከሚነሱ ጥቅሞች የመጀመሪያዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(3) መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ለክርክር ማንሳት ነው። የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያዎች በተቻለ መጠን በቶሎ መቅረብ ያለባቸው ሲሆን ይህም የሚሆነው በጽሑፍ መልስ ላይ በመሆኑ የጽሑፍ መልስ አለማቅረብ ይህንን መብት ያሳጣል። ሌላኛዉ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 234 (1) መሠረት የጽሑፍ መልስ ሊይዛቸው ከሚችላቸው ውስጥ ለቀረበው ክስ መከላከያ የሚሆኑትን የሰነድም ሆነ የሰው ማስረጃዎችን መዘርዘር ያለበት በመሆኑ መልስ አለማቅረብ ይህንንም ያሳጣል።[65] በመሆኑም ተከሳሽ በዚህ ቀጠሮ ቀን ካልቀረበ ክርክሩን በጽሑፍ የማቅረብ፣ የማስረጃ ዝርዝር የማቅረብ እና የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር የማቅረብ መብቱን ያጣል። ነገር ግን ክሱ በሚሰማበት ቀን በክርክሩ ዉስጥ ይቀጥላል።[66] ከዚህ ዉጪ "እንደከሳሹ ሊጠየቅ ይችላል፣ መስቀለኛ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል ወ.ዘ.ተ።"[67]

---

[62] መንበረፀሐይ 79.
[63] ዝኒ ከማሁ.
[64] Rabner and Grant 12-1.
[65] መንበረፀሐይ 80.
[66] ዝኒ ከማሁ.
[67] ዝኒ ከማሁ.

ከዚህም በመነሳት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67፣ 70፣ 73 እና ሌሎች ተዛማጅ ድንጋጌዎች እንደሚያመላክቱት ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱም ጉዳዩ ለመሰማት (hearing) በተቀጠረበት ቀን ያልቀረቡ እንደሆነ ብቻ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ (እንደነገሩ ሁኔታ ይግባኝ ባይ) ወይም ተከሣሹ (እንደነገሩ ሁኔታ የይግባኝ መልስ ሰጪ) ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ለሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የሚሆን ሌላ የሕግ ድጋፍ መኖር ይኖርበታል። የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት የመ/ቁ.14184 እና 15835 ስር መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ጊዜ ፍ/ቤት ለክንዋኔዉ መሠረት ማድረግ ያለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ ከ222-240፣ 192-199 ያሉት ድንጋጌዎች በተለይ 233፣ 194፣ 199 መሆኑን አስገንዝቧል።[68] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ ከ222-240 ያሉት ድንጋጌዎች በፍ/ቤት የመጀመሪያዉ ክርክር ሂደት የክርክሩን የክስና መልስ አቤቱታ ተከራካሪዎች እንዲያዉቁት ማድረግ ነዉ። የሕጉ ቁጥር 199(1) *‹‹ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈጸም የቀረው ከተከራካሪ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ የጉዳዩን መፈጸም ሳይጠብቅ በዚያው ቀነ ቀጠሮ የመሰለውን ውሳኔ ለመስጠት ይችላል›› ይላል።* እንዲሁም የሕጉ ቁጥር 194 *"በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን ያለበት ድርጊት በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልተከናወነ ዋጋ እንደሌለው ይገለፃል።"* የሕጉ ከቀጥር 192 እስከ ቁጥር199 ያሉት ድንጋጌዎች ከቁጥር 233 ጋር አብሮ ሲነበብ ለመልስ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሹ መልሱን ካላቀረበ ፍ/ቤቱ የጽሑፍ መልስ ለመቀበል ሌላ ቀጠሮ ሳይሰጥ ወደሚቀጥለዉ ደረጃ መቀጠል አለበት ወደሚለዉ ድምዳሜ ይወስደናል።[69] በዚህም መሠረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘ ተከሣሽ መልሱን ከማቅረብ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጥቅሞች ይቀርበታል እንጂ ከክሱ እንዲወጣ አይሆንም። እንዲሁም ቁጥር 233 ስር የተደነገገዉ default proceeding ለዚሁ ዓላማ እንደሚዉል የእንግሊዘኛዉ ቅጂ የተሻለ ግልፅነት እንዳለዉም በፌ/ጠ/ፍ/ሰ/ሰ/ችሎት ተመላክቷል።[70] ሌላዉ ጉዳይ ተከሳሽ መልስ ባለማቅረቡ ወይም እራሱ ባለመቀረቡ የከሳሽን

---

[68] አቶ ውርጌሳ ታደሰ *v* አቶ መለሰ ተካ; ሼል የኢትዮጵያ አ/ማ *v* በወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ.

[69] መንበረፀሐይ 79.

[70] ሼል የኢትዮጵያ አ/ማ *v* በወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ.

ክስ እንዳለ መቀበል(ቀጥታ ወደ ዉሳኔ መሄድ) ተገቢ ስላልሆነና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 241 በአጭር ሥነ ሥርዓት ከሚታዩ ጉዳዮች ዉጪ ተግባራዊ ስለሚሆን የከሳሽ ክስ የሕግ ድጋፍ ያለዉ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡[71] በዚህ ክፍል በሦስተኛነት መዳሰስ ያለበት ሌላዉ ጉዳይ መልስ ለመቀበል በተሰጠ ቀጠሮ ከሳሽ ቢቀር ዉጤቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለዉ ነዉ፡፡ ቀደም ብሎ እንደተዳሰሰዉ ሕጉ ጉዳዩ ለመሰማት በተያዘ ቀጠሮ ተከራካሪዎች ባይቀርቡ ስለሚወሰደዉ እርምጃ ከሚደነግግ በቀር ክስ ለመቀበል በተሰጠ ቀጠሮ ተከራካሪዎች ባይቀርቡ ስለሚወሰደዉ እርምጃ የሚለዉ የለም፡፡ በተግባር ፍ/ቤቶች በዚህ ቀጠሮ ከሳሽ ሳይቀርብ በሕጉ ስለ ክስ መስማት የሚመለከቱትን ድንጋጌዎች በመጠቀም በቁጥር 69 (2) መሠረት የክሱን መዝገብ መዝጋት ወይም በቁጥር 73 መሠረት ጉዳዩን(ክሱን) መዝጋት እንደ ችግር የሚነሳ ነዉ፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67፣ 70፣ 73 እና ሌሎች ተዛማጅ ድንጋጌዎች ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱም ጉዳዩ ለመሰማት (hearing of parties) በተቀጠረበት ቀን ያልቀረቡ እንደሆነ ብቻ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ለሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የሚሆን ሌላ የሕግ ድጋፍ መኖር ይኖርበታል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ 192-199 ባሉት ቁጥሮች ፍ/ቤት እንዲፈፀሙ ያዘዛቸው ጉዳዮች ሳይፈፀሙ ሲቀሩ ስለሚሰጡ ትዕዛዞች የተለያዩ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ በቁጥር 199 ሥር ያለው ድንጋጌ አሁን ለያዝነው የክስ መልስ ለመቀበል ስለተሰጠ ቀጠሮ በተለይ አግባብነት ያለው ነው፡፡ በዚህ የሕጉ አንቀጽ ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በዚያው ቀነ ቀጠሮ የመሰለውን ውሣኔ ለመስጠት ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር (2) ደግሞ ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው በተከራካሪዎቹ ወገኖች ጉድለት ያልሆነ እንደሆነ ግን ፍ/ቤቱ ሌላ ቀጠሮ ይሰጣል ይላል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ፍ/ቤቱ እንዲፈፀም ያዘዘዉ ነገር ሁሉ ፍ/ቤቱ ባስቀመጠዉ ጊዜ ዉስጥ

[71] መንበረፀሐይ 80; Mary Kay Kane, *Civil Procedure* (4th edn, West Publishing Co., 1996) 165 [Here after Kane].

መከናወን እንዳለበት እና ፍ/ቤቱ አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበለት በስተቀር ተጨማሪ ጊዜ እንደማይሰጥ ማሳያ ናቸው፡፡[72]

በዚሁ ቀጠሮ በልዩ ሁኔታ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር ከከሳሽ በኩል መልስ ከመቀበል በቀር የሚከወን ተግባር አለመኖሩ፤ ከሳሽ መልስ አለመቀበሉ በፍ/ቤቱ ስራ ላይም የሚያደርሰዉ መስተጓጎል ባለመኖሩ በቁጥር 69(2) መሠረት የክሱን መዝገብ መዝጋቱ ወይም በቁጥር 73 መሠረት ጉዳዩን (ከሱን) መዝጋቱ ተክክል አይደለም፡፡[73] ምክንያቱም ቁጥር 69(2) ክስ በሚሰማበት ቀን ሁለቱም ወገኖች ካልቀረቡ የሚፈም እና ቁጥር 73 ክስ(ጉዳዩ) በሚሰማበት ቀን ከሳሽ ካልቀረበ የሚመለከት በመሆኑ ነዉ፡፡[74] *በአቶ ውርጌሳ ታደሰ እና አቶ መለሰ ተካ* መካከል በነበረው ክርክር መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ጊዜ ከሳሽ ባለመቅረቡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዝገቡ እንዲዘጋ መወሰኑ በተግባር ለሚታየዉ ችግር በምሳሌነት የሚጠቀስ ነዉ፡፡ ይህም የሕጉን ድንጋጌ በተቃረነ መልኩ የተሰጠ ነዉ፡፡ በዚህ ጉዳይ በመ/ቁ 14184 የስር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት እንደሚከተለዉ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

> *‹‹ በመሠረቱ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ የሚያዘው በአንድ ጉዳይ ክስ የተመሠረተበት ሰው በጉዳዩ ላይ የቀረበበትን ክስ ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ ሃሣቡን በጽሁፍ እንዲያቀርብ ማስረጃም ካለው የማሰረጃውን ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ እንዲያቀርብ ለማድረግ ነው፡፡ <u>በመሆኑም ከከሣሹ የሚጠበቅ ክንዋኔ የለም፡፡ ከሣሹ ሳይቀርብ ቀረ እንኳን ቢባል በፍርድ ቤቱ የሥራ ሂደት ላይ የሚያስከትለው መስተጓጐል ሊኖር አይችልም፡፡</u> በመሆኑም መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ባይቀርብ የተከሣሹን መልስ ተቀብሎ ለተከታዩ ክንውን ጉዳዩን ከማዘጋጀት አልፎ መዝገቡን ለመዘርጋት በቂ ምክንያት የለም (empahasis added by the author)፡፡››[75]*

[72] ዝኒ ከማሁ 79.

[73] ዝኒ ከማሁ 78.

[74] ዝኒ ከማሁ.

[75] አቶ ውርጌሳ ታደሰ *v* አቶ መለሰ ተካ 53.

ከሳሽ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን ባለመቅረቡ ክሱ (ጉደዩ) ሊዘጋበት አይችልም ይልቁንም የክስ መልሱን በመጣበት ቀን መዉሰድ ይችላል፡፡ ምክንያቱም በዚሁ ቀጠሮ በልዩ ሁኔታ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር መልስ ከመቀበል ሌላ የሚከወን ተግባር አለመኖሩ፤ ከሳሽ መልስ አለመቀበሉ በፍ/ቤቱ ስራ ላይም የሚያደርሰዉ መስተጓጎል ባለመኖሩ ነዉ፡፡[76] ሥለዚህ ክሱ በሚሰማበት ቀጠሮ ተፈፃሚ እንዲሆኑ የተደነገጉትን የሕጉ ደንቦች የተለየ ባህርይና ዓላማ ባለው የተከሳሽን መልስ የመቀበል ቀነ ቀጠሮ ተፈፃሚ ማድረግ አግባብነት የለውም፡፡ በመሆኑም የሕጉን ክፍተት ለመሙላት አግባብነት ያለዉ በሕጉ ቁጥር 192-199 ይመስላል፡፡ [77] ፍ/ቤቱም እነዚህን ድንጋጌዎች እንደሁኔታዉ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን ተከሳሽና ከሳሽ ሁለቱም ፍ/ቤት ባይቀርቡ ምን ዉጤት ያስከትላል የሚለዉን እናያለን፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 192-199 በተለይም ቁጥር 199 እና ከላይ በተሰጠዉ ማብራሪያ መሠረት በዚህ ቀጠሮ ሁለቱም ተከራካሪዎች ፍ/ቤት ባይቀርቡ ፍ/ቤቱ የመሰለዉን ዉሳኔ መስጠት ከሚችል በቀር ሌላ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ፍ/ቤቱ እንዲፈፀም ያዘዘዉ ነገር ሁሉ ፍ/ቤቱ ባስቀመጠዉ ጊዜ ዉስጥ መከናወን እንዳለበት እና ፍ/ቤቱ አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበለት በስተቀር ተጨማሪ ጊዜ እንደማይሰጥ ይደነግጋሉ፡፡ ለምሳሌ ከሳሽ ጉዳዩን ለመከታተል እንዳልፈለገ ተቆጥሮ መዝገቡን መዝጋት ወይም ፍ/ቤቱ ቀጠሮዉን ሊያራዝም ይችላል፡፡ ይህ ሚሆንበት አግባብም ከሳሽ ቢቀርብ ኖሮ ተከሳሽ ባይቀርብም ፍ/ቤቱ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ መሆኑን በመገንዘብ ክሱ የሚሰማበትን ቀጠሮ ለመስጠት ያስችለዉ ስለነበር ነዉ፡፡ ከሳሽ በዚህ ቀጠሮ ባይቀርብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) መሠረት መዝገብ አይዘጋም፡፡ ምክንያቱም በዚሁ ቀጠሮ በልዩ ሁኔታ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር ከከሳሽ በኩል መልስ ከመቀበል በተጨማሪ የሚከወን ተግባር አለመኖሩ ከሳሽ መልስ አለመቀበሉ በፍ/ቤቱ ስራ

[76] መንበረፀሐይ 78.

[77] ዝኒ ከማሁ.

ላይም የሚያደርሰዉ መስተጓጎል ባለመኖሩ ነዉ::[78] ሌላኛዉ ምክንያት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) ክስ ለመስማት የሚሰጥ ቀጠሮን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ ነዉ።

## 3.2. ክሱ የሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ

በዚህ ክፍል ክስ(ጉዳዩ) ለመስማት በተሰጠ ቀጠሮ የፍ/ቤቱ ክንዋኔ ምንድን ነዉ የሚለዉ ተብራርቷል። እንዲሁም በዚህ ቀጠሮ ከተከራካሪዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ባይቀርቡ የሚከተለዉን ዉጤት ተመላክቷል። ክስ የሚከፈትበትና የሚሰማበትን ሥነ-ሥርዓት ሥንመለከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 241 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በርካታ ክንዋኔዎች ይፈፀማሉ። በዚህ ቀጠሮ ተከራካሪዎች ስለጉዳዩ በራሳቸዉ አንደበት የሚያብራሩበት፤ ፍ/ቤቱም የተከራካሪዎችን የመሰማት(የመደመጥ) መብት በጉልህ የሚተገብርበት ነዉ። በዚህ ቀጠሮ ፍ/ቤት ከሚያከናውናቸው ተግባራት የተወሰኑት በዚህ ጽሑፍ ተዳሰዋል። ፍ/በቱ በመጀመሪያ ባለጉዳዮች ወይም ተወካዮቻቸው ለችሎት መቅረባቸውን ያረጋግጣል። በመቀጠልም ክሱን እና መልሱን ለግራ ቀኙ በንባብ ያሰማል። ይህም ተግባር በዋነኝነት ተከራካሪ ወገኖች ክስና መልሱ ትክክለኛው ግልባጭ እንደደረሳቸው ለማረጋጥ ይረዳል። በሶስተኛ ደረጃም በተሟጋቾች የጽሑፍ ክስ እና መልሱ ላይ በቀጥታ ወይም በነገሩ አካባቢ ሁኔታ እንደተካደ የሚቆጠረውን ነገር የሚያምን ወይም የሚክድ መሆኑን ተከሳሹን ወይም ወኪሉን በጥያቄ ይመረምራል።[79] ክስ የሚሰማበት ቀጠሮ ፍ/ቤቱ አከራካሪዉን ጉዳይ(ጭብጥ) የሚለይበት፣ በተካደዉ ላይ ማመንን የሚያገኝበት፣ አላስፈላጊ ጉዳዮችን የሚቀንስበትና ሙግቱን የሚያሳጥርበት እንዲሁም ጉዳዩን ለሙግት (trial) ለማድረስ የመጨረሻዉ ደረጃ ነዉ።[80]

የዚህ ቀጠሮ ሕግ መሠረታዊ ዓላማ ተከራካሪ ወገኖች በጽሑፍ ያቀረቡትን ክርክር ለማብራራትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 446-448 መሠረት ጭብጥ ለመመስረት እንዲያግዝ

---

[78] ዝኒ ከማሁ.

[79] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241(1).

[80] Balew and Mizane 234.

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl

መሆኑን የፌ/ጠ/ፍ/ቤትሰ/ሰ/ችሎት *በሙሉ ኤሌክሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማሕበር እና ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል /ኢ.አ/* መካከል በነበረዉ ክርክር ላይ አብራርቷል። [81] በዚህ የቃል ምርመራ ፍ/ቤቱ ማንኛውንም እምነት እና ክህደት በመዝገብ ላይ በጽሑፍ እንዲሰፍር ያደርጋል። በመቀጠልም አከራካሪ የሆነውን ፍሬ ነገር፣ ጭብጥ በመለየት ተከራካሪ ወገኖች እንዲያዉቁት ብሎም በማስረጃ አንጥሮ ለመወሰን ለቀጣዩ ቀጠሮ ያዘጋጃል። የአንድ ጉዳይ አከራካሪ ጭብጥ ከሳሽ በክስ የገለጸዉና ተከሳሽ ክዶ የተከራከረበት ነጥብ ነዉ።[82] ከዚህ በተጨማሪ ተከራካሪዎች ክርክራቸዉን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚገደዱበትና ፍ/ቤቱ በተካራካሪዎች የቀረበዉን ማስረጃ ተዓማኒነትና ክብደት የሚመዝነዉ ግራ ቀኙ ተካክደዉ በሚከራከሩበት ጭብጥ ላይ ብቻ ነው። ከሳሽና ተከሳሽ ያልተካካዱበትና ከሳሽ በክሱ ገልፆ ተከሳሽ ባመነዉ ነጥብ ላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ማስረጃ በመመዘን ሣይሆን ተከሳሹ በሰጠዉ የእምነት ቃል ወይም መልስ መሠረት መወሰን እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 242 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ በመመርመር መረዳት ይቻላል።

ይህም ክስ ለመስማት በተያዘ ቀጠሮ ፍ/ቤት የመጨረሻ ዉሳኔ ሊሰጥ እንደሚችል ያስገነዝባል። በዚህ ቀነ ቀጠሮ ፍ/ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በጽሑፍ መልሱ ላይ ተከሳሹ አቅርቦ ከሆነ በቅድሚያ የከሳሹን አስተያየትና ክርክር በማዳመጥ ብይን ይሰጣል።[83] በታመኑት ጉዳዮች ላይ እንዲሁ ውሳኔ ይሰጣል። ተከራካሪ ወገኖች በሕግም ሆነ በፍሬነገሩ የሚለያዩበት ወይም የሚያከራክራቸዉ ጉዳይ ያለመኖሩን ፍ/ቤት የተገነዘበ እንደሆነ ወይም ተከራካሪ ወገኖች ነገሩን በስምምነት የፈቱት እንደሆነ ተጨማሪ ማስረጃ ማስቀረብ ሳያስፈልግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 253-254 መሠረት በዚህ ቀጠሮ ቀን ዉሳኔ ይሰጣል። ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስቀርብ ከሆነ ይህ ሂደት ፍ/ቤቱ ባለጉዳዮችን ጭምር በማነጋገር

[81] [2005 ዓ] 15 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 160

[82] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246.

[83] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 244(1).

ጉዳዩን ለዋናው ክርክር እና የማስረጃ መስማት ደረጃ የሚያዘጋጅበት በመሆኑ የከሳሹና ተከሳሹ (ወኪሎቻቸው) መገኘት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡[84]

በተያዘ ቀጠሮ የቃል ክርክር ማድረግና የመልስ ሰጭን የጽሑፍ መልስ መቀበል በክርክር ሂደት ሁለቱም እራሳቸውን የቻሉ ሥርዓቶች እንጂ አንዱ ሌላውን ሊተካ የሚችል ወይም ተመሳሳይ የክርክር ደረጃዎች አይደሉም፡፡ የሁለቱም ሥርአት አፈፃፀም የሚያስከትለው ውጤት የተለያየ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ ቀጠሮ የቃል ክርክር ማድረግና የመልስ ሰጭን የጽሐፍ መልስ መቀበል ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም፡፡[85]

በዚህ ክፍል የተዳሰሰዉ ሌላዉ ጉዳይ ክርክሩ (ክሱ) በሚሰማበት ቀጠሮ የተከራካሪዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱም በችሎት አለመገኘት የሚያስከትለው ውጤትን መለየት ነዉ፡፡ ሕጉን ስንመለከት የክስ መስማት የሚመለከተው የሙግት ሂደት ፍ/ቤቱ ባለጉዳዩችን በማነጋገር ጉዳዩን ለዋናው የሙግት/trial/ ደረጃ የሚያዘጋጅበት በመሆኑ የከሣሹና ተከሣሹ ወይም የወኪሎቻቸው መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡[86] ከሁለቱ የአንዱ አለመገኘት ለሂደቱ መስተጓጐል የሚኖረው ተፅዕኖም ከፍተኛ ነው፡፡[87] በመሆኑም ከሌሎች ቀጠሮዎች በተለየ መልኩ ባለጉዳዩች ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ባይቀርቡ የሚከተለው ውጤት ከሌላው የበለጠ ጠንካራ መሆኑ አስፈለጊ ነው፡፡[88] ከላይ ካየነዉ መልስ ለመቀበል ከሚሰጠዉ ቀጠሮ ይልቅ ሕጉ ጥብቅ እርምጃ አስቀምጧል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ምዕራፍ 2 (ከቁጥር 241 - 273) ያሉት ሁሉም ድንጋጌዎች የተሟጋቾች አለመገኘት የሚያስከትለውን ውጤት

---

[84] Sedler *183, Para. 2.*

> "In general, at first hearing, the court reads the statement of defence, examines both parties to determine their respective positions, rules on any preliminary objections, and frames the issues for trial. In certain circumstances, the court may adjudicate the case at the first hearing without requiring a full-scale trial. If the proceeding is transferred to the trial stage, the court sets a date for the trial and at the trial it hears evidence and decides the issues."

[85] የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ *v* አቶ ታረቀኝ ገ/ፃዲቅ [2001] 9 ፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት*,* መ/ቁ 36380*,* 16.

[86] መንበረፀሓይ 78.

[87] ዝኒ ከማሁ.

[88] ዝኒ ከማሁ.

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl

ከመሰማት ሂደት ጋር ተያይዞ የቀርቡትም በከፊል በዚህ ምክንያት ነው። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) እና ተከታይ ድንጋጌዎች በመሰማት ሂደት ከተሟጋቾች አንዱ (ሁለቱም) አለመገኘት የሚያስከትለውን ውጤት በሚመለከት አግባብነት አለዉ። ይህም እንደሚቀጥለዉ ተብራርቷል።

በመጀመሪያም ክሱ በሚሰማበት ቀጠሮ ተከሳሽ ካልቀረበ ዉጤቱ ምን ይሆናል የሚለዉ ተመላክቷል። በዋናነት ተከሳሽ ክስ በሚሰማበት ቀን ካልቀረበ ክርክሩ በሌለበት እንዲሰማ ፍ/ቤቱ እንደሚያዝ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 70 ላይ በግልፅ ተደንግጓል። ይህ ሲሆን ፍ/ቤቱ በቅድሚያ ለተከሳሽ መጥሪያ በተገቢው ሁኔታ መድረስ አለመድረሱን ያረጋግጣል። ተከሳሽ ያልቀረበው መጥሪያ ደርሶት መሆኑ ከተረጋገጠ ክርክሩ በሌለበት መሰማት ይቀጥላል። ይህም በእንግሊዘኛዉ ቅጂ Ex-parte Proceeding ተብሎ ይጠራል። ክርክሩ ተከሳሽ በሌለበት ይከናወናል ስንል ተከሳሽ ከክርክር ሂደቱ ዉጭ ይሆናል ማለት ነዉ። ይህም ማለት በቃል መከራከር፣ ምስክር የማሰማት፣ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ እና የመሳሰሉት መብቶችን ያጣል።[89] ተከሳሽ ወይም ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ብይን መስጠቱ ፍርዱ ለከሳሽ በሚጠቅም መንገድ የመወሰኑን ሁኔታ በአስገዳጅነት የሚያስከትል እንዳልሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70(ሀ) ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መረዳት ይቻላል።[90] በመሆኑም ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት ይታይ ሲባል ክርክር በአንድ ወገን ብቻ ይሆንና ፍ/ቤቱ የከሳሽን አቤቱታ ካደመጠ በኋላ ሕግን መሠረት አድርጎ ለከሳሽ የሚገባዉ መብት ካለ ይወሰንለታል፤ ካለሆነ ግን ለተከሳሽ ሊወሰንለት ይችላል።[91] "The mere absence of the defendant does not of itself justify the presumption that the plaintiff claim or case is true."[92] በሌላ አገላለጽ

[89] ዝኒ ከማሁ 80.

[90] በዩሊስ ቡራሌ ሲጋል የራይስ ጫት ላኪዎች ማህበር v አቶ አብዲ አልሚ መሓመድ [2005] 14 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 144.

[91] Danishah Farudnji, Mulla, *Code of Civil Procedure Act V of 1908* (12th ed., the Eastern Law House,1953) 566. [Here after Mulla); Kane 167; Sedler 163-164.

[92] Mulla 566.

ክሱ ተከሳሽ በሌለበት እንዲሰማ ብይን ተሰጠ ማለት ክርክሩ ለከሳሽ ይወሰናል ማለት አይደለም።[93]

የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 70(ሀ)) መግቢያ (‘ክርክሩ እንዲሰማ’ ስለሚል) የሚያመላክተዉ ተግባራዊነቱ በመጀመሪያ የክስ መሰማት ክንዉን እንጂ በሌላ የፍ/ቤቱ ቀጠሮዎች ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ነዉ።[94] በመሆኑም ዓላማዉ ክስ ለመስማት ካልሆነ ፍ/ቤቱ በሚሰጠዉ ማንኛዉም የፍ/ቤት ቀጠሮ ተከሳሽ ወይም መልስ ሰጪ ባይቀርብ በሌለበት (ex-parte) ክሱ ይሰማ ሊባል አይችልም::[95] በተግባር ግን ፍ/ቤቶች ከዚህ በተቃራኒዉ ሲተገብሩ ይስተዋላል። [96] ለምሳሌ *በወይዴ ሎንዶም እና ዘዉዲቱ ተክለገወርጊስ* መካከል በነበረዉ ክርክር የቀደዳ ገመል ወረዳ ፍ/ቤት ማስረጃ ለመመርመር (ክስ ለመመርመር) በያዘዉ ቀጠሮ ተከሳሽ ባለመቅረቡ ምክንያት ክሱ በሌለበት እንዲሰማ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70(ሀ) መሠረት ብይን ሰጥቷል።[97] የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70(ሀ) ተግባራዊ የሚሆነዉ ክሱን ለመስማት በተያዘ ቀጠሮ ነዉ በማለት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ ሽሮታል። እንዲሁም *በሼል ኢትዮጵያ አ/ማ እና በወ/ሮ አስቴር ብርሃነስላሴ* ክርክር ጉዳይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መልስ ለመቀበል በተያዘ ቀጠሮ ተከሳሽ ባለመቅረቡ ክሱ በሌለበት እንዲታይ በመወሰኑ ተመሳሳይ ችግር ተስተዉሏል።[98]

ከላይ እንደተገለፀዉ ተከሳሽ በሌለበት ክርክር እንዲቀጥል ብይን ለመስጠት ተከሳሽ መጥሪያ በአግባቡ የደረሰዉ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።[99] ነገር ግን መጥሪያ በትክክል መድረሱ ያልተረጋገጠ ከሆነ ፍ/ቤቱ ሁለተኛ መጥሪያ ለተከሳሹ ያ’ዛል ወይም ተከሳሽ መጥሪያዉ

---

[93] Sedler 163-164.
[94] Balew and Mizane 219.
[95] ዝኒ ከማሁ 200; መንበረፀሓይ 78-79.
[96] Kane 167.
[97] [1990] 14 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት.መ/ቁ 74/90.
[98] ሼል የኢትዮጵያ አ/ማ *v* በወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ዉሳኔ ሽሮታል.
[99] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር70 (ሀ).

ዘግይቶ የደረሰዉ ከሆነ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣል፡፡[100] ሆኖም ግን በተግባር ፍ/ቤቶች ለተከሳሽ መጥሪያ በአግባቡ መድረስ አለመድረሱን ሳያረጋግጡ በዚህ ቀጠሮ ካልቀረበ በሌለበት እንዲታይ ብይን ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ *በዳዊት ተስፋዬ እና አሚና መሃመድ*[101] እንዲሁም *በፀሐዬ ባህታ እና አዛለች ቸነሬ*[102] መካከል በነበረዉ ክርክር የስር ፍ/ቤት ተከሳሽ በችሎት ያልቀረበዉ መጥሪያ በአግባቡ ደርሶት መሆን አለመሆኑን ሳያረጋግጥ በሌለበት እንዲታይ ብይን ሰጥቷል፡፡ ፍ/ቤት ተከሳሽ ያልቀረበዉ መጥሪያዉ በአግባቡ ሳይደርሰዉ የሆነ እንደሆነ ሁለተኛ መጥሪያ ለተከሳሽ እንዲደርሰዉ ወይም መጥሪያ የደረሰዉ መልስ ለማዘጋጀት በቂ ባልሆነ ቀን ከሆነ የቀጠሮ ቀኑን በማራዘም ጉዳዩ በሌላ ቀን እንዲታይ ከማድረግ በቀር ተከሳሽ በሌለበት ክሱ አይሰማም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌላዉ ማብራሪያ የሚያሻዉ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ብይን ሲሰጥ ለተከሳሹ ምን አማራጮች አሉት የሚለዉ ነዉ፡፡ ተከሳሹ በቀጠሮው ባለመቅረቡ ምክንያት በሌለበት ክርክሩ እንዲሰማ ከተደረገ በኋላ ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለ (while the case is pending) በሚቀጥለው ቀጠሮ ቀርቦ በቀዳሚው ቀጠሮ ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል (sufficient cause) ምክንያት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ፣ ፍ/ቤቱም ከተቀበለው በቀረበበት ቀን መከላከያውን አቅርቦ እንዲከራከር ሊፈቅድለት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 72 ላይ ተደንግጓል፡፡ የሕጉ ዓላማ ተከሳሽ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ከክርክሩ ዉጪ እንዳይሆን፣ እራሱን እንዲከላከል ማስቻል ነዉ፡፡ "The right to be heard in a suit is one of the important principles of the natural justice."[103] የኢትዮጵያ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ይህን መርህ በአግባቡ አካቷል፡፡ በዚህ ሕግ አንቀፅ 72 በአማርኛና እንግሊዘኛ ቅጂዉ መካከል ልዩነት ያለ ሲሆን የአማርኛ ቅጂዉ ተከሳሹ የክስ

---

[100] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 70 (ለ-ሐ).

[101] [1988] የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት የመ/ቁ 2132/99.

[102] [1988] የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ/ቁ 1658/88.

[103] Naresh Kumar, 'Ex parte Decree and its remedies || Order 9 Rule 13 || CPC ||' (August 19 2019) <https://www.lawnotes4u.in/ex-parte-decree-and-its-remedies-order-9-rule-13-cpc/> accessed on August 24 2021.

መልስ ያላቀረበ ከሆነም እንዲያቀርብ በመፍቀድ በግልፅና በተሻለ ሁኔታ የተከሳሹን መብት ያስጠብቃል፡፡

በተጨማሪም ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ዉሳኔ ወይም ትዕዛዝ ተሰጥቶበት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78(1-2) መሠረት በቃል ለመከራከር በቂ ሆኖ በሚገመት ምክንያት አለመቻሉን ዉሳኔዉ ወይም ትዕዛዙ መሰጠቱን ካወቀ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ ለፍ/ቤቱ በማስረዳት ይህን ዉሳኔ ወይም ትዕዛዝ ማስነሳት ይችላል፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቱ ለከሳሽ ጉዳዩን ማሳወቅና ስለወጪ የመሰለዉን በመወሰን ዉሳኔዉን ወይም ትዕዛዙን ያነሳዋል፡፡[104] በዚህ ሕግ የአንድ ወር ጊዜ ገደቡ የሚሰላዉ ተከሳሹ ዉሳኔ ወይም ትዕዛዝ መሰጠቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ እንጂ የዉሳኔዉን ወይም የትዕዛዙን ይዘት ማወቅ አለማወቅ አላግባብ ለፍትህ መዘግየት እንዳይዳርግ ሲባል ከግምት አይገባም፡፡

በተግባር በዚህ ጉዳይ የተለያየ ልምድ በፍ/ቤቶች ዘንድ አጋጥሟል፡፡ ለምሳሌ፡ *በራሄል ወልደማርያም እና በእነ ዝናየነሽ እና ሌሎች* መዝገብ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሳሽ በሌለበት የተላለፈዉን ዉሳኔ እንዲሰረዝ ያመለክታል፡፡ ሆኖም ግን የተከሳሽ ጠበቃ ዉሳኔ እንደተሰጠ ካወቀ ከአራት ወር ስለበለጠዉ ፍ/ቤቱ የአንድ ወር የጊዜ ገደቡ አልፏል በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማማልከቻዉን ዉድቅ ሲያደርገዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤቱን ዉሳኔ የተከሳሽ ጠበቃ ዉሳኔዉን የሰማበትን ትክክለኛ ቀን አልተረጋገጠም በማለት ይሽረዋል፡፡[105] የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ የአንድ ወር የጊዜ ገደቡን ለማስላት ተከሳሽ ስለዉሳኔዉ መስማቱ ከተረጋገጠ በቂ ነዉ፤ የዉሳኔዉን ይዘት አላወቅሁም ነበር በሚል ማስተባበል ያላግባብ ፍትህ እንዳይዘገይ ያግዛል ሲል ወስኗል፡፡[106] በሌለበት ዉሳኔ የተሰጠበት ተከሳሽ ያለው አማራጭ ይግባኝ ማቅረብ ነዉ፡፡[107]

---

[104] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78(2).

[105] በራሄል ወልደማርያም *v* በእነ ዝናየነሽ እና ሌሎች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁ 19087.

[106] በራሄል ወልደማርያም እና በእነ ዝናየነሽ እና ሌሎች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ/ቁ 015084.

[107] የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲ *v* ሙሉጌታ ተስፋኮረስ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ/ቁ 13839.

በሦሥተኛ ደረጃ ክርክሩ (ክሱ) በሚሰማበት ቀጠሮ የከሳሽ ፍ/ቤት አለመቅረብ የሚያሰከትለዉን ዉጤት እናያለን። የተከራካሪ ወገኖች ቀጠሮ አለማክበርን በሚመለከት የሚደነግግ ሕግ ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የተቀላጠፈ ፍትሕ እንዲሰፍን ያለመ ነዉ። በመሆኑም ተከሳሽ ቀርቦ ከሳሽ ክሱ በሚሰማበት ቀጠሮ ካልቀረበ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት ችሎቱ ሁለት አይነት ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይችላል። አንደኛ ተከሳሽ ቀርቦ በተከሰሰበት ፍሬ ነገር ላይ በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ በሙሉ ወይም በከፊል በታመነዉ ጉዳይ ላይ የፍርድ ውሳኔ ይሰጣል።[108] ሁለተኛ ተከሳሹ በሙሉ የካደ እንደሆነ ከሳሽ ከፍ/ቤቱ ለማግኘት የጠየቀውን መብት የተወው መሆኑን በመረዳት ክሱን ይዘጋዋል (dismissal of the case) ።[109] ምክንያቱም ከሳሽ የጉዳዩን ክርክር ወደሚሰማበት ችሎትበመቅረብ የበኩሉን አልተወጣም፣ በቀጠሮወ አልተገኘም እንዲሁም ጉዳዩ እንዲዘገይ አድርጓል።[110] ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀጠሮ ካልቀረበ እና ተከሳሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ጉዳይ በሙሉም ሆነ በከፊል ካመነ ከሳሽ በሌለበትም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ባመነው ጉዳይ የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችል እና ተከሳሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት እንደሚያሰናብተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ላይ ተመልክቷል። ይህ ድንጋጌ በይግባኝ ክርክር ላይ ጭምር ተፈፃሚ መሆኑ በቁጥር 32(2) ድንጋጌ ስለተመላከተ የይግባኝ ቅሬታው በሚሠማበት ቀጠሮ ይግባኝ ባይ ካልቀረበ ተፈፃሚነት ያለው ይኸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 ነው። ስለዚህ

---

108 የኢትዮጵያ ልማት ባንክ *v* ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰሌጠኛ ማዕከል [2002] 9 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 280 (ከዚህ በኃላ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ *v* ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ተብሏል):

> ‹‹.... *በተያዘው ጉዳይ ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ይግባኝ ባይ የነበረው አመልካች ሳይቀርብ ተጠሪ ቀርቧል።በዚህ መሠረት ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሳይቀርብ ተከሳሹ ቀርቦ ክሱን በከፊል ወይም በሙሉ ያመነ ከሆነ ላመነው ጉዳይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መስጠት እንደሚችልና ከካደ ደግሞ መዝገቡ እንደሚዘጋ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ያመለክታል። በዚህም ምክንያት አግባብነበት የሚኖረው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 እንጂ ቁጥር 69(2) አይደለም። በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሔ/ቁ 69(2) አግባብነት የሚኖረው ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሁለቱም ተከራካሪዎች ያልቀረቡ ከሆነ ነው።›› ሲል ወስኗል።*

109 ዝኒ ከማሁ.

110 Kane 169.

የክሱ መዝገብ መዘጋት የሚወሰነው ተከሳሽ ለቀረበበት ክስ ከሚሠጠው መልስ አኳያ ታይቶ ነው ማለት ነው። በመሆኑም ተከሳሽ የቀረበውን ክስ መካድ ማመኑ ሣይረጋገጥ መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቁ ብቻ መዝገቡ ሊዘጋ እንደሚችል ድንጋጌው አያመለክትም።[111]

ሆኖም ግን በተግባር ከሕጉ መንፈስ ዉጪ ሲከወን ይስተዋላል። ለምሳሌ፡ *በኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት እና ትግራይ ዱቄትና የምግብ ዝግጅት ፋብሪካ*[112] መካከል በነበረዉ ክርክር የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ክስ ለመስማት በሰጠበት ቀጠሮ ሁለቱም ተከራካሪዎች ቀርበዉ ተከሳሽ ጉዳዩን በስምምነት እንደፈቱት በማሳሰብ ስምምነቱን ለማቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጥ ጠይቆ በተሰጠዉ ተለዋጭ ቀጠሮ ዕለት ከሳሽ ባለመቅረቡ ፍ/ቤቱ የተከሳሽን የእምነት ክህደት ቃል ከአቤቱታዉ ሳያገናዝብ ክሱን ይዘጋዋል። ይህ ተግባር ከሕጉ ድንጋጌ የራቀ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ሽሮታል።[113] ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚነሳዉ የክስ መዘጋት ብይን ለመስጠት ፍ/ቤቱ በቅድሚያ የተከሳሽን የእምነት ክህደት ቃል መቀበል እንዳለበት ተመላክቷል። ነገር ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ተከሳሽ ያቀረበዉን አቤቱታ የሚክድበትና የሚያምንበት ሁለት ዕድል አለዉ። የመጀመሪያዉ የክስ መልስ አቤቱታዉ ላይ በጽሑፍ[114] ሲሆን ሁለተኛዉ በክስ መሰማት ቀን በቃል ነዉ።[115] ነጥቡ ተከሳሹ በክስ መልስ አቤቱታዉ ላይ በጽሑፍ ያመነዉን ጉዳይ በክስ መሰማት ቀን የከሳሽን አለመቅረብ እንደ ዕድል ተጠቅሞ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ቢክድ ፍ/ቤቱ ለሚወስነዉ ብይን መሠረት ማድረግ የሚገባዉ መቼ የተሰጠዉን የተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃል ነዉ የሚለዉ ነዉ። በዚህ ጊዜ እንግዲህ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 235 እና 241 ስንመለከት ቀድሞ በመልሱ ላይ የታመነ ጉዳይ ሊካድ እንደማይችልና በክስ መሰማት ቀን ተከሳሹ የእምነት

---

111 የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን *v* እነ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድይፍራው (ሁለት ሰዎች) [2001] 8 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 73.

112 የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት *v* ትግራይ ዱቄትና የምግብ ዝግጅት ፋብሪካ [1992›] የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ/ቁ.1/92.

113 የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት *v* ትግራይ ዱቄትና የምግብ ዝግጅት ፋብሪካ [1992] የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ/ቁ.5023/92.

114 በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 235.

115 ዝኒ ከማሁ ቁጥር 241.

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl

ክህደት ቃሉ የሚጠየቀው ቀድሞ በተካደዉ ጉዳይ ላይ ብቻ ነዉ፡፡[116] ሥለሆነም ተከሳሽ የከሳሽን በዚህ ቀጠሮ አለመቅረብ ተጠቅሞ ቀድሞ ያመነዉን መካድ አይችልም፤ ከሳሽ በዚህ ቀጠሮ በመቅረቱ ስለሚከተለዉ ዉጤት ለመወሰንም ከግምት አይገባም፡፡[117]

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት የሚሰጥ የክስ መዝጋት ዉሳኔ (order of dismissal of the suit) የሚተገበረዉ ክስ ለመስማት በተሰጠ ቀጠሮ ከሳሽ ቢቀር በመሆኑ በሌሎች የፍ/ቤቱ ቀጠሮዎች ላይ ተግባራዊ አይሆንም። ምክንያቱም ክስ ለመስማት የሚሰጥ ቀጠሮ ፍ/ቤቱ ለክርክሩ መሳለጥ ወሳኝ ተግባራትን ለመከወን የተከራካሪ ወገኖች መገኘት ቀጥተኛ ተፅዕኖ በመኖሩ የተከራካሪዎች በዚህ ቀጠሮ ፍ/ቤት አለመቅረብ ጠንከር ባለ እርምጃ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ ነዉ፡፡[118] ሆኖም ግን በተግባር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት የክስ መዝጋት ብይን በሌሎች የፍ/ቤት ቀጠሮዎች ከሳሽ ሲቀር ሲጠቀሙት ይስተዋላል። ለምሳሌ፣ *በናስር መሀመድ እና እነ የገቢዎች ቢሮ* መካከል በነበረዉ ክርክር የአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በድህነት እንዴት ሊቀርብ እንደቻለ ለመመርመር በተያዘ ቀጠሮ ከሳሽ በመቅረቱ ክሱ (ጉዳዩ) እንዲዘጋ የሰጠዉን ዉሳኔ መመልከት ይቻላል፡፡[119] እንዲሁም *በወርጊሳ ታደሰ እና መለሰ ተካ እና ሌሎች* መካከል በነበረዉ የይግባኝ ክርክር የተጠሪን የይግባኝ መልስ በጽሑፍ ለመቀበል በተያዘ ቀጠሮ አመልካች ባለመገኘቱ ክሱ እንዲዘጋ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ዉሳኔ ሌላዉ ምሳሌ ነዉ::[120]

ሌላዉ ነጥብ ክሱ የተዘጋበት ከሳሽ ክሱን ለማስቀጠል ምን የመፍተሔ አማራጮችን አሉት የሚለዉ ነዉ። ክሱ ከተዘጋ በኋላ ከሳሽ ለክሱ መነሻ የነበረውን ጉዳይ መሠረት በማድረግ በድጋሜ አዲስ ክስ ለማቅረብ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74 ላይ ተገልጿል። ይህ ክልከላም ከሳሽ በአንድ ሰረ-ነገር ሁለት ጊዜ ክስ ማቅረብ አይቻልም ከሚለዉ ዋና መርህ ነዉ

---

116 ዝኒ ከማሁ ቁጥር 233-234, 223.

117 ዝኒ ከማሁ ቁጥር 241.

118 መንበረፀሓይ 78.

119 በናስር መሀመድ *v* በእነ የገቢዎች ቢሮና ሌሎች የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.1624.

120 በወርጊሳ ታደሰ *v* መለሰ ተካ እና ሌሎች.

የወጣዉ፡፡[121] ነገር ግን ከሳሹ ያልቀረበው ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ የተዘጋው ክስ እንደገና ተከፍቶ ከቆመበት እንዲቀጥል ሊደረግ እነደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74(2) ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የተፈጥሮ የፍትሕ መርሕ የሆነዉን የመሰማት መብት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

በተጨማሪም ከአቅም በላይ በሆነ እክል ምክንያት ፍ/ቤት በቀጠሮዉ መቅረብ ያልቻለ ከሳሽ እና በቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ ያልቀረበን ከሳሽ እኩል ማስተናገድ የሕጉ ዓላማ እንዳልሆነ ያስገነዝባል፡፡ ከሳሹ በቀዳሚው ቀጠሮ ያልቀረበዉ በቂ ሆኖ የሚገመት እክል ምክንያት በመግለጽ ከሱ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል:: ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ከተቀበለዉ ስለኪሳራው እና ስለወጪ አከፋፈል ከወሰነ በኃላ የተዘጋው ክስ እንዲቀጥል ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡[122] ይህ ድንጋጌ ከሳሹ በቀጠሮው ያልቀረበዉ በቂ ሆኖ የሚገመት እክል ምክንያት መሆን እንደሚገባው ከመግለጽ ውጪ በቂ ሆኖ የሚገመት እክል ውስጥ የሚካተቱት ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡ ይልቁንም ሕጉ የመረጠዉ ከአቅም በላይ የማያስብሉትን ሁኔታዎች መዘርዘር ነዉ፡፡ *በዚህም መሠረት በስራ ብዛት፣ በመዘንጋት፣ በቸልተኝነትና በራሱ ጉድለት መሆኑ በታወቀ ጊዜ እንደ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት እንደማይቆጠርና አዲስ የጊዜ መራዘም ዉሳኔ እንደማይሰጠዉ ህጉ ያስገነዝባል፡፡*[123] ይህም የሚቀርብላቸውን አቤቱታ ከድንጋጌው ይዘት እና ዓላማ አንፃር መርምሮ ተገቢውን ዳኝነት የመስጠት ኃላፊነት ለፍ/ቤቶች የተተወ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ሆኖም ግን ይህን አስመልክቶ በተግባር ብዙ ችግር ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ፡ *በተክለብርሃን ተክለሃይማኖት እና ደብረምህረት ቅድስ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን*[124] መካከል በነበረዉ

---

[121] Mulla 570.

[122] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ ቁጥር 74(2).

[123] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 196(3).

[124] *በተክለብርሃን ተክለሃይማኖት v ደብረምህረት ቅድስ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን የድሬዳዋ ፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት* በመ/ቁ. 96189.

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl

ክርክር የድሬዳዋ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ ከስ በሚሰማበት ቀን በመቅረቱ ክሱን የዘጋዉ ቢሆንም ከሳሽ ያልቀረበዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ስላስረዳ ብይኑ ተነስቶለታል። ነገር ግን የክስ መዘጋት ብይን ይነሳልኝ አቤቱታዉ የቀረበዉ የአንድ ወር የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ ነበር። በሕጉ ቁጥር 74(2) የአንድ ወር ጊዜ ገደብ እና በቂ ምክንያት ቅድመሁኔታዎች አብረዉ (complementary conditions) መሟላት አለባቸዉ።

በመሆኑም ፍ/ቤቱ ሕጉ ከሚፈቅደዉ ዉጪ ተግብሯል። በፍ/ቤቶች በልማድ እንደ በቂ ምክንያት የሚቆጠሩ ሁኔታዎችን በሚከተሉት ምሳሌዎች ማየት ይቻላል። *በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና በአበበች ዘዉዱ*[125] መካከል በነበረዉ ክርክር የትራፊክ መዘጋጋት እንደ በቂ ምክንያት /sufficient cause/ አይቆጠርም በማለት የአመልካችን የክስ መዘጋት ብይን ይነሳልኝ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉድቅ ቢያደርገዉም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የትራፊክ መጨናነቅ እንደ በቂ ምክንያት ይቆጠራል ሲል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔን ሽሮታል።[126] በሌላ ጉዳይም *በእነ ወ/ሮ ብዙ ሰንበታ/ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ታደሰ ሰንበታ*[127] መካከል በነበረዉ ክርክር አመልካቾቹ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በነበራቸው ክርክር መዝገቡ በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ አመልካቾቹ በዚያኑ ቀን በ4፡ 30 ሰዓት ፍ/ቤት የደረሱ መሆናቸውን እና በሰዓቱ መንገድ በመዘጋጋቱ ምክንያት መሆኑን ገልጸው ቢከራከሩም በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት ፍ/ቤቱ አቤቱታዉን ውድቅ አድርጓል። ሆኖም ግን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካቾቹ ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስላቸው አቤቱታ ያቀረቡት መዝገቡ በተዘጋ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑ ሲታይ ጉዳያቸውን በአግባቡ በመከታተል ላይ የነበሩ መሆኑን እና በሰዓቱ በቀጠሮው ሳይገኙ የቀሩትም በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት (መንገድ መዘጋጋት) በመሆኑ

---

[125] በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ *v* በአበበች ዘዉዱ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ/ቁ 1218/95.

[126] በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ *v* በአበበች ዘዉዱ, የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት, የመ/ቁ 12654.

[127] በእነ ወ/ሮ ብዙ ሰንበታ/ሁለት ሰዎች/ *v* አቶ ታደሰ ሰንበታ [2007 ዓ.ም] 17 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 13.

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ74(2) መሠረት ተቀባይነት ሊሰጠው እንደሚገባም ወስኗል፡፡ ይህም የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74(2) ለመተርጎም አንዱ ምሳሌ ነዉ፡፡[128]

በተጨማሪም *በወ/ሮ ሳኒያ ከድር እና የኮሪያ ዘማቾች ቤተሰቦች ሽመናና ስጋጃ ስራ*[129] መካከል በነበረው ክርክር አመልካች /የስር ከሳሽ/ ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን እንደማንኛውም ሰው በፍ/ቤት ቅጥር ጊቢ ዉስጥ ተራዋን በመጠባበቅ ላይ እያለች በስህተት የሌላ ሰው መዝገብ ሲጠራ ወደ ችሎት ገብታ የእርሷ ያልሆነው መዝገብ ሲዘጋ የእርሷ ጉዳይ የተዘጋ መስሏት ወደቤት በመሄዷ የእርሷ መዝገብ ሲጠራ መቅረብ አልቻለችም፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪዎች በንቃት መከታተል ያለባቸዉ በመሆኑ ይህ አይነቱ ምክንያት እንደበቂ እክል አይቆጠርም፤ መዝገቡም ሊንቀሳቀስ አይገባም ብሎ ይወሰናል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት በበኩሉ ይህ አይነቱ አጋጣሚ በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብለው ጉዳያቸውን ትተው የሄዱ ናቸው ወደ ሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አለመሆኑን በመገንዝብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74(2) ድንጋጌ መሠረት እንደ በቂ የእክል ምክንያት ተቆጥሯል፡፡ *በዞን ሁለት የገንዘብ ቢሮ እና በአቶ ከበደ ሙስጦፋ*[130] መካከል በነበረዉ ክርክር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጠበቃዉ ባለጉዳዩን ሳያሳዉቅ ዉሉን በማቋረጡ ከሳሽ ቢቀር ጠበቃዉ ባለጉዳዩን አለማሳወቁ ከሳሽ ለመቅረቱ እንደ በቂ ምክንያት እንደሚቆጠር ኣሳይቷል፡፡

አንድ ተከራካሪ ወገን ፍ/ቤት በቀጠሮ ቀን በችሎት ሰዓት መቅረት ወይም ዘግይቶ መገኘቱ በቂ በሆነ የእክል ምክንያት ነዉ ለማለት ተከራካሪዉ ወገን ሆን ብሎ ነዉ ወይም በራሱ ቸልተኝነት ነዉ በሚያስብል ሁኔታ መሆን የለበትም፡፡ ሥለዚህ ተከራካሪ ወገን በቀጠሮ ቀን የቀረዉ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነና በቀጠሮ ቀን ፍ/ቤት ለመድረስ በቂ የሚባል ጥረት ካሳየ ይህ እንደ በቂ ምክንያት የሚቆጠር ነዉ፡፡ ሆኖም ግን ሕጉ አሁን ካለዉ ድንጋጌ በተለየ እንዴት መዉጣት ነበረበት የሚለዉ የሕግ አወጣጥ መርሆችን መመርመር አስፈላጊ

---

[128] ዝኒ ከማሁ .

[129] በወ/ሮ ሳኒያ ከድር *v* የኮሪያ ዘማቾች ቤተሰቦች ሽመናና ስጋጃ ስራ [2006 ዓ.ም] 16 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 15.

[130] በዞን ሁለት የገንዘብ ቢሮ *v* በአቶ ከበደ ሙስጦፋ, የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት, መ/ቁ. 1052/98.

ቢሆንም ሕጉ ከአቅም በላይ የሆነ እክል የሚባሉትን ነገሮች ለመዘርዘር አለመሞከሩ ለትርጉምና በዳኞች ይሁንታ ላይ እንዲንጠለጠል መፍቀዱ ከባድ ችግር ፈጥሯል።

በአራተኛነት ክሱ በሚሰማበት ቀጠሮ የከሳሽና ተከሳሽ ሁለቱም ፍ/ቤት አለመቅረብ የሚያስከትለዉ ዉጤት ምንድነዉ የሚለዉ ነዉ። ሁለቱም ተከራካሪዎች ካልቀረቡ በከሳሽ ወይም ተከሰሽ በአንደኛዉ ላይ ብቻ እርምጃ ለመዉሰድ ያስቸግራል።[131] ሁለቱም ተሟጋቾች ክርክሩ በሚሰማበት ቀጠሮ ያልቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) መሠረት መዝገቡን መዝጋት ይችላል:: ክስ በሚሰማበት ቀጠሮ ፍ/ቤቱ ሁለቱንም ወገን በማነጋገር ለዋናዉ የሙግት ጊዜ ዝግጅት ስለሚያደርግ የተከራካሪዎች የሁለቱም አለመገኘት ብዙ ነገር ያስተጓጉላል።[132] ሆኖም ግን በተግባር አንዳንድ ችግሮች እንዳሉ ባይዘነጋም *የፌ*/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት *በኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ሰላም የቴክኒክና ሙያ ማሰሌጠኛ ማዕከል* መካከል በነበረዉ ክርክር ሁለቱም ተከራካሪዎች ያልቀረቡ እንደሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) አግባብነት እንዳለዉ አመላክቷል፤ ዉጤቱም ክሱን መዝጋት ነዉ።[133] ለዚህ ዋናዉ ምክንያትም ተከሳሽ ቢቀር እንኳ ከሳሽ ቀርቦ የክሱን ዉጤት አለመከታተኩ፤ እንዲፈረድለት ያመለከተዉን ጉዳይ ላይ የሚሰጠዉን የፍርድ ዉጤት አለመፈለጉን ስለሚያመላክት ነዉ። በዚህ ቁጥር መሠረት የመዝገቡ መዘጋት የሚያስከትለዉን ዉጤት ቀደም ብሎ ስለተብራራ እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም።[134]

በመጨረሻም ከክስ/ጉዳዩ/ መዘጋት ጋር ተያይዞ ግልፅ ማድረግ የሚያስፈልገዉ የክስ መዘጋት (order of dismissal) እና የመዝገብ መዘጋት (struck out) መካከል ያለዉን ልዩነት ነዉ። የክስ መዘጋትን በተመለከተ በዚህ ንዑስ ክፍል ከላይ በሠፊዉ ስለተብራራ መድገሙ አስፈላጊ ስለማይሆን የመዝገብ መዘጋት መቼ ይሰጣል የሚለዉን በመመልከት ልዩነታቸዉን

[131] Sime 353.
[132] መንበረፀሐይ 78.
[133] የኢትዮጵያ ልማት ባንክ *v* ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰሌጠኛ ማዕከል.
[134] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 71.

እናያለን። ለዚህ መሠረት የምናደርገዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2)፣ 70(መ)፣ 71፣ 73፣ 74 ድንጋጌዎች በማየት ነዉ። የሕጉ በእነዚህ ድንጋጌዎች የአማረኛና እንግሊዘኛ ቅጂ መለያየት ለችግሩ መንስኤ ነዉ። የአማርኛዉ ቅጅ የመዝገብ መዘጋትን ብቻ ነዉ የሚጠቀመዉ። "(...) ፍ/ቤቱ መዝገቡን ይዘጋዋል።"[135] "(...) የክስ መዝገብ ዘግቶ/የይግባኙን መዝገብ ለመዝጋት ይችላል::"[136] "የክስ መዝገብ መዝጋት"[137]፣ "(...) መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተዋል"[138] በማለት የእንግሊዘኛዉን ቅጂ "dismissal" and "Struck out" በተመሳሳይ ቃል መተካቱ በክስ (ጉዳዩ) መዘጋት (dismissal) እና በመዝገብ መዘጋት (struck out) መካከል ያለዉ ልዩነት ብዥታ ፈጥሯል።

የመዝገብ መዘጋት (struck out) ብይን የሚከተለዉ በሁለት ምክንያቶች ነዉ። አንደኛዉ በቁጥር 69(2) መሠረት ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቱ በሰጠዉ ቀጠሮ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ያልቀረቡ እንደሆነ ሲሆን ሌላኛዉ በቁጥር 70 (መ) መሠረት ከሳሽ ለተከሳሽ በቸልተኝነት ወይም በራሱ ጉድለት (ለምሳሌ፡ ባለጉዳዩ ሆን ብሎ ክርክሩን ለማዘግየት ወይም በቸልተኝነት) መጥሪያ ያልሰጠዉ እንደሆነና ተከሳሽ በቀጠሮዉ ካልቀረበ ነዉ። የመዝገብ መዘጋት (struck out) የሚያስከትለዉ ዉጤት በጊዜያዊነት መዝገቡ ተዘግቶ እንዲቆይ ሲሆን ከሳሹ በቂ ምክንያት ካቀረበ ያለተጨማሪ የፍ/ቤት ክፍያ ክርክሩ ይቀጥላል።[139] ከሳሽ በቂ ምክንያት ማቅረብ ካልቻለ የፍ/ቤት ክፍያ በመክፈል ክሱን በአዲስ መዝገብ መጀመር ይችላል።[140]

ስለዚህ በመዝገብ መዘጋት (struck out) ጊዜ ከሳሽ በቂ ምክንያት አቀረበ አላቀረበም ድጋሜ በጉዳዩ ላይ አዲስ ክርክር እንዳያቀርብ አያግደዉም፤ ብቸኛ ልዩነቱ የፍ/ቤት ክፍያ ድጋሜ መክፈሉ ላይ ነዉ። አዲስ መዝገብ የሚከፈት ከሆነ የተዘጋዉ መዝገብ እንዳልተከፈተ

[135] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 69(2).
[136] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 70(መ).
[137] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 71.
[138] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 73.
[139] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 71(2).
[140] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 71(1).

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl

ተቆጥሮ አዲሱ ክስ የይርጋ ጥያቄ ሊነሳበት ይችላል፡፡[141] በአንፃሩ በክስ (ጉዳዩ) መዘጋት (dismissal) ፣ ክስ በሚሰማበት ቀጠሮ ከሳሽ ባይቀርብ የሚከተል ዉጤት ሲሆን በዚህ ጊዜ ከሳሽ በቂ ምክንያት አልቀረበም\አላቀረበም በተመሳሳይ ጉዳይ አዲስ ክስ (fresh suit) እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም፡፡[142] በክስ መዘጋት ጊዜ ከሳሽ ሊያደርግ የሚችለዉ በቂ ምክንያት ካለዉ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በማቅረብ የፍ/ቤትና ሌላ ወጭም ካለ በመክፈል ጉዳዩ እንዲቀጥል ማድረግ ነዉ፡፡[143]

## 3.3. ማስረጃ ለመስማትና ምስክሮችን ለመመርመር በተሰጠ ቀጠሮ

በዚህ ክፍል ማስረጃ ለመስማትና ምስክሮችን ለመመርመር በተሰጠ ቀጠሮ የፍ/ቤቱ ክንዋኔ እንዲሁም ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱ ባይቀርቡ የሚያስከትለዉ ዉጤት ተብራርቷል፡፡ የፍ/ቤት ክንዋኔን በተመለከተ በዚህ ቀጠሮ ቀደም ሲል የተመለከተዉን ሂደት እና በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር ሁኔታዎች ተግብሮ አከራካሪውን ጉዳይ መፍትሔ መስጠት ሳይችል ሲቀርና አከራካሪ የሆነውን ፍሬ ነገር በጭብጥ መልኩ ከያዘ በኋላ እልባት ለመስጠት ማስረጃ በማስቀረብ የሚሰማበት እና የሚመረምርበት ቀጠሮ ሲሆን ማስረጃ እንዲያሰማ የተፈቀደለት ተሟጋች ማስረጃዉ የሚሰማበትን ነጥብ ለይቶ ለችሎቱ ያሰማል፡፡[144]

---

[141] Sedler 165. “Moreover, it is as if the first action had not been instituted, so if the statute of limitations has expired before he institutes the second suit, that suit will be hatred by limitations.”

[142] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 74(1).

[143] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 74(2). See also, Sedler 166፡

> “[The applicant] may apply, within one month from the date of the dismissal, for an order to set the dismissal aside, and if he can show that there was sufficient because for his non-appearance, the order of dismissal is set aside, and the court will proceed with the suit by holding the hearing originally scheduled. In other words, where there was sufficient cause for the non-appearance, the court will hold the hearing originally scheduled and proceed therefor. But, if he does not apply -in time or the court finds that there was not, sufficient cause for his non-appearance, he is forever bared from prosecuting the claim.”

[144] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 258-59.

በአንድ የፍትሐ-ብሄር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲለይ የሚደረገው እና ማስረጃ የሚደመጠው ተከራካሪ ወገኖች የተለያዩበት (ያልተስማሙበት) ነጥብ ላይ ነው፡፡ ይህም ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 246፣ 247፣ 248፣ 256፣ እና ሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ማንኛውም የክርክር ጭብጥ ሁልጊዜ በማስረጃ እንዲነጥር የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሆኖ ተከራከሪ ወገኖች በተለያዩባቸውና ዳኝነት በሚሹ ነጥቦች ላይ ከሚሰማ በስተቀር በማንኛውም ፍሬ ነገር ላይ እንዲሰማ የግድ የሚል የማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን ደንብ የለም፡፡ ከሁሉም በላይ ማስረጃ እንዲሰማለት የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን ማስረጃው የሚሰማበትን ጭብጥ ለይቶ የማስረጃውን አይነትና የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በመጥቀስና በእጁ ላይ ያለውን ማስረጃም አያይዞ ማቅረብ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223፣ 234፣ 137(3)፣ 145፣ 256 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡[145]

አንድ ሰው ክስ የማስረዳት ወይም የመከላከል ሕጋዊ መብት ያለው ሲሆን ፍ/ቤት ይህንኑ መብቱን ሊያልፍ የሚገባው ተከራካሪዉ ወገን የቆጠረው ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን እርግጠኛ ሲሆን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223፣ 234፣ 137፣ 249 እና 256 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡[146] በመሆኑም ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው የማስረጃ አቀራረብና ምዘና ሥነ-ሥርዓቱ በሚያስቀምጠው መንገድ ተከናውኖ መሆኑን እነዚህ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ተከራካሪ ወገን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ ቆጥሮ እያለ ማስረጃ ሳይሰማ ፍርድ መስጠት የመከራከር መብቱን የሚያጣብብ ነው፤ ውሳኔውም ሕጋዊ ሥርዓቱን ተከትሎ ተሰጥቷል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በተከራካሪ ወገን የተቆጠረውን ምስክር ሁሌ ፍ/ቤቱ እንዲሰማ የማይገደድ ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለማስረጃ አቅራረብ እና አቀባበል የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝበን ነጥብ ሲሆን ፍ/ቤቱ ይህንኑ

---

[145] እነ አቶ እንድሪስ አደም/5 ሰዎች/ *v* ወ/ሮ አስናቀች ጥላሁን [2005] የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት, የመ/ቁ 77983, 87.

[146] It is related to the concept of relevance and admissibility of evidence.

ስልጣኑን መተግበር ያለበት በዘፈቀደ ሊሆን አይገባም። በዚህ መሠረት ክሱ ወይም መልሱ ላይ የተዘረዘሩት የሰዉም ሆነ የሰነድ ማስረጃዎች አግባብነት እና ተቀባይነት የለውም ካልተባለ በስተቀር በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ከተገኘ፣ ማስረጃ እንዲሰማ የሚፈልግ ተከራካሪ ወገንም ማስረጃው የሚሰማበትን ነጥብ ለይቶ ካቀረበ ማስረጃ ወይም ምስክር ሳይሰማ የሚታለፍበት አግባብ የለም።

ሆኖም ግን በተግባር ፍ/ቤቶች ይህን ስለማስረጃ የተሰጡ ድንጋጌዎች ሲጥሱ ማየት የተለመደ ነዉ። ለምሳሌ *የገቢ ዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር*[147] መካከል በነበረዉ ክርክር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የአመልካችን ማስረጃ (የዋጋ ዝርዝር መረጃ በጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ ጉዳዩን ለማስረዳት የተቆጠሩት ምስክሮችንም) መስማት አስፈላጊ አለመሆኑን ገልፆ ጉዳዩን በመመርመር የተከሳሽን ክርክር ውድቅ አድርጎ የክርክሩ ባለዕዳ አድርጎታል። ሆኖም ግን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት በተከራካሪ ወገን የተቆጠሩ ምስክሮች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለጉዳዩ የሚሰጡት ምስክርነት አግባብነት /relevance/ የሌለዉ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ በመሆኑ ተከራካሪዎች በሥነ-ሥርአቱ መሠረት ማስረጃዎቻቸውን ዘርዝረው አቅርበው እያለ የቆጠሯቸው የሰነድና የሰው ምስክሮች ሳይታዩና ሳይሰሙ ማስረጃ አልቀረበም በሚል በዘፈቀደ ዉሣኔ ሊሰጥ አይገባም በማለት ሽሮታል።

*በእነ መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና መምህር ሲሳይ ደጀኔ ጥላሁን*[148] *መካከል* በነበረዉ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ተከሳሽ የስራ ውል የተቋረጠበትን ምክንያት በመከላከያ መልስ ማመልከቻው ላይ ከመግለፃቸውም በተጨማሪ ይህንኑ ፍሬ ነገር ለማስረዳት የሰነድና የሰው ማስረጃዎቻቸውን በመከላከያ ማስረጃው መግለጫ ዝርዝር ላይ ጠቅሰው፣ የሰነድ ማስረጃዎችንም አያይዘው እያለ የቆጠሯቸውን የሰው ምስክሮች

---

[147] [2002 ዓ.ም] 9 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 320.

[148] [2002 ዓ.ም] 9 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 50.

ለማቅረብ ያልቻሉ መሆኑ ሳይረጋገጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በደፈናዉ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ወስኗል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት ተከሳሽ የስንብት ደብዳቤዉ ላይ የገለፀዉን ምክንያት ለማስረዳት የቆጠረውና አግባብነት ያለው ማስረጃ ሊሰማለትና ሊመዘንለት ሲገባ ይኸው ሥርአት ሳይከናወን የሚሰጥ ፍርድ የተሟላ አካሄድ ተከትሎ የተሰጠ ነው ሊባል የማይችልና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት ሽሮታል፡ ፡

ይህንን በሚመለከት ዶ/ር መንበረፀሃይ ታደሰ የፍ/ቤቶች አሰራር ሕጉ ከሚለዉ ያፈነገጠበት ሌላዉ ዓብይ ጉዳይ የምስክሮች አቀራረብ መሆኑን ገልፀዋል፡፡[149] ከችግሮች ዉስጥ አንደኛዉ ምስክሮችን በመስማት ሂደት በከፊል ፍ/ቤቶች ምስክር ከመጥራታቸዉ በፊት ጭብጥ አለመያዛቸዉ የማስረዳት ሸክም ማን ላይ እንደሚወድቅ አለመለየት፣ ባለጉዳዮች የሚጠሩዋቸዉ ምስክሮች በሙሉ የመጥራትና ጭብጥ ባልሆነ ጉዳይ ላይ እንዲመሰክሩ መደረጉ ነዉ፡፡[150] ከዚህ በተጨማሪ ምስክር የሚሰማዉ በተለያየና በጣም በተራራቀ ጊዜ መሆኑ (የከሳሽ መስክር መጀመሪያ ይቀርብና የተከሳሽ ደግሞ ሌላ ጊዜ መሆኑ) ፣ የአንዱ ወይም የሌላዉ ምስክር ተሟልቶ አልቀረበም እየተባለ የሚሰጠዉ ተጨማሪና ተደጋጋሚ ቀጠሮ እና ለምስክሩ በቂ አበል አለማስያዝን የሚመለከት ነዉ፡፡[151] ይህም ልማድ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር መጣረሱ ሳያንስ የፍርድ መዘግየት፣ የተዛባና አድሏዊ ፍርድ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡[152]

ከዚህ በመቀጠል ማስረጃ ወይም ምስክር በሚሰማበት ቀን የአንዱ ወይም የሁለቱም በፍ/ቤት ቀጠሮ ሳይገኙ መቅረት የሚያስከትለዉ ዉጤት በሚመለከት ተብራርቷል፡፡ በመጀመሪያ የከሳሽ ምስክሮች በሚሰሙበት ቀጠሮ ከተካራካሪዎች የአንዱ ወይም የሁለቱም አለመቅረብ ምን ዉጤት ይኖረዋል? የሚለዉን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ነዉ፡፡

---

[149] መንበረፀሐይ 74.

[150] ዝኒ ከማሁ 75-76.

[151] ዝኒ ከማሁ 74, 76.

[152] ዝኒ ከማሁ.

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl

አንደኛ ፍ/ቤቱ የከሳሽን ምስክሮች ለመመርመር ቀጠሮ በያዘበት ዕለት ከሳሽ ምስክሮቹን አቅርቦ ሳለ ተከሳሽ ካልቀረበ ተከሳሹ መስቅለኛ ጥያቄ የመጠየቅና በጥያቄ አቀራረቡ ሂደት መቃወሚያ/objection/ የማንሳት መብቱን ብቻ ያጣል፡፡[153] ይህም ተከሳሽ የክርክሩ አሸናፊ የመሆን እድሉ ይጣበባል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 263(3) መሠረት መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ ምስክሩ የሰጠውን ቃል ሀሰት ማስባል ወይም እውነታነቱን በሚያጠራጥር ሁኔታ ፍ/ቤቱ እንዲረዳው የማድረግ መብቱ ይቀርበታል፡፡[154] ከዚህ በተጨማሪም በምስክሩ የጥያቄ አቀራረብ ላይ የሚቀርበውን መቃወሚያ የማንሳት መብቱም ይቀርበታል፡፡[155] በክርክር ሂደት ዉስጥ መቃወሚያ ከሚነሳባቸዉ ምክንያቶች ምስክር ያቀረበዉ ተከራካሪ ወገን መሪ ጥያቄ (leading questions) ለምስክሩ በመጀመሪያ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ነዉ፡፡[156] መሪ ጥያቄ የሚባለዉ ተከራካሪዉ በተዘዋዋሪ ምስክሩ ምን ማለት እንዳለበት ሲነግር (መልሱን የሚያመላክት ጥያቄ) ነዉ፡፡ ይህ እዉነትን የሚደብቅ፣ የፍትህ ስርዓቱንም የሚያዛባ ጥያቄ አይነት በመሆኑ ከመግቢያ ጉዳዮች እና ፍ/ቤት በሚፈቅደዉ መሠረት ሌሎች ዉስን ጉዳዮች ካልሆነ በቀር መሪ ጥያቄ መጠየቅ ሕጉ ይከለክላል፡፡[157] ለዚህ ምክንያቱም ምስክሩ በስሜት ህዋሱ የተገነዘበዉን ብቻ ለፍርድ ቤቱ ስለጉዳዩ በራሱ አንደበት እንዲያስረዳ ለማስቻል ነዉ፡፡[158]

ሁለተኛ የከሳሽን ምስክር ለመመርመር በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ በእርሱ ጉድለት (ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት) መስከሮችን ለችሎቱ ካላቀረበ ምን ሕጋዊ ዉጤት ይኖረዋል? የሚለዉ

---

[153] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ - ቁጥር 199(1).

[154] Sedler *203-204*. "During cross-examination, the opponent tries to discredit that testimony of witnesses and persuades the court that it should not believe their testimony." It is about "impeaching credibility" of witness testimony.

[155] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 270.

[156] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 163(2) ‹‹ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ በቀር በማናቸዉም ሁኔታ ለሚመሰከረዉ ጉዳይ መሪ የሚሆን ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም፡፡››

[157] ዝኒ ከማሁ. See also, Sedler 203. Sedler mentions setuations the court may at times permit the asking of leading questions. 1) When the witness is being examined as to what are called 'introductory matters', 2), to refreashe the memory of witnesses, 3) to assist child witness.

[158] Sedler 203, Para. 4. The testimony must genuinely be that of the witness and not the examiner; the examiner cannot put words in the mouth of the witness, so to speak.

ነዉ። የከሳሽን ምስክር ለመመርመር በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ ምስከሮችን ለችሎቱ ካላቀረበ እና ይህም በእርሱ ጉድለት የሆነ እንደሆነ ምስክር የማሰማት መብቱ ይታለፍበታል።[159] የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት በ*አቶ ውርጌሳ ታደሰ እና አቶ መለሰ ተካ ጉዳይ* ላይ በሰጠው የሕግ ትርጓሜ ፍ/ቤት እንዲፈፀሙ ያዘዛቸው ጉዳዮች ላይ ስለሚሰጡ ትዕዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ ከ192 እስከ 199 ባሉት ቁጥሮች መሠረት መሆኑን አመላክቷል።

በቁጥር 199(1) መሠረት ለቀጠሮው ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ሳይፈፅም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛዉ ጉደለት የሆነ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳን ፍ/ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በያዘው ቀጠሮ የመሰለውን ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችል ይደነግጋል። ፍ/ቤቱም ምስክር ማቅረብ የነበረበት ባለጉዳይ በራሱ ጉድለት (ባለጉዳዩ ሆን ብሎ ክርክሩን ለማዘግየት በማሰብ ወይም በቸልተኝነት) ምክንያት ምስክሮቹን አስቀርቦ ካላስመሰከረ ምስከር የማሰማት መብቱ ይታለፍበታል። በዚህ ጉዳይ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል። *በእነ ወ/ሮ ሸዋዬ ገ/እግዚአብሔር እና ወይንሸት መንግስቱ*[160] መካከል በነበረዉ ክርክር ሁለቱም ተከራካሪዎች በተገኙበት ምስክር ለመስማት በተያዘው የቀጠሮ ቀን ሌላ ቀጠሮ ነበረኝ በሚል ምክንያት የአንድ ወገን ጠበቃ አለመቅረብ በቂ ምክንያት እንዳልሆነ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል።ከዚህ መረዳት የምንችለዉ ከሳሽ ማስረጃ በሚያቀርብበት ቀጠሮ ያለበቂ ምክንያት ካልቀረበ ማስረጃ የማቅረብም ሆነ ምስክር የማሰማት መብቱ ይታለፍበታል የሚለዉን ነዉ። እንዲሁም ተከሳሽ ክዶ ከተከራከረ የከሳሽ ክስ ዉድቅ ይደረግበታል። ተከሳሽ ካመነ ግን ባመነዉ መሠረት ፍ/ቤቱ ዉሳኔ ይሰጣል። ለዚህ ዉሳኔ መሠረት የሆነዉ የሕግ ድንጋጌም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199(1) ነዉ።[161]

---

[159] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 199(1).

[160] [2010] 22 የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት 60.

[161] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 199(1) ሥር እንደተደነገገው *"ለቀጠሮ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት ሆኖ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ*

ቀደም ሲል የከሳሽ ምስክሮች በሚሰሙበት ቀጠሮ ከተካራካሪዎች የአንዳቸዉ መቅረት ምን ዉጤት እንዳለዉ አይተናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የተከሳሽ ምስክሮችን ለመስማት በተያዘ ቀጠሮ ከተካራካሪዎች የአንዳቸዉ መቅረት ምን ዉጤት እንዳለዉ እንደሚቀጥለዉ ተብራርቷል፡፡ አንደኛ ፍ/ቤቱ የተከሳሽን ምስክሮች ለመመርመር ቀጠሮ በያዘበት ዕለት ተከሳሽ እና ምስክሮቹ ቀርበው ከሳሽ ካልቀረበ ፍ/ቤቱ የተከሳሽ ምስክሮችን ከሳሽ በሌለበት የምስክርነት ቃላቸው በመቀበል ይመረምራል፡፡ ይህም ከሳሽ የክርክሩ አሸናፊ የመሆን እድሉን ያጣብባል፡፡ ምክንያቱም ተከሳሽ የሆነ ሰዉ የከሳሽ ምስክሮች በሚሰሙበት ጊዜ አለመገኘቱ ምስክሮቹን መስቀለኛ ጥያቄ (Cross Examininination) የመጠየቅ እንዲሁም በጥያቄ አቀራረቡ ሂደት መቃወሚያ (objection) ማንሳት እንደማይችል ሁሉ ከሳሽ የሆነ ሰዉ የተከሳሽ ምስክሮች በሚሰሙበት ቀጠሮ አለመገኘቱ ምስክሮቹን መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ እንዲሁም በጥያቄ አቀራረቡ ሂደት መቃወሚያ ማንሳት አይችልም ማለት ነዉ፡፡ ይህም ከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ ምስክሩ የሰጠውን ቃል ሀሰት ማስባል ወይም እውነታነቱን በሚያጠራጥር ሁኔታ ፍ/ቤቱ እንዲረዳው የማድረግ መብቱ ይቀርበታል፡፡[162] እንዲሁም በምስክሩ የጥያቄ አቀራረብ ላይ የሚቀርበውን መቃወሚያ የማንሳት መብቱንም ያጣል፡፡[163]

ሁለተኛ የተከሳሽን ምስክር ለመመርመር በተቀጠረበት ቀን ተከሳሽ ምስከሮችን ለችሎቱ ማቅረብና ማስመስከር ሲገባዉ ካላቀረበ እና ይህም በእርሱ ጉድለት የሆነ እንደሆነ ምስክር የማሰማት መብቱ ይታለፍበታል፡፡[164] የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት በመ/ቁ 14814 ላይ በሰጠው የሕግ ትርጓሜ ፍ/ቤቱ እንዲፈፀሙ ያዘዛቸው ጉዳዮች ላይ ስለሚሰጡ ትዕዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 192-199 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት መሆኑን እና በቁጥር 199 (1)

---

*ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳ ፍ/ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ የመሰለውን ውሳኔ መስጠት እንደሚችል ተመልክቷል፡፡"*

[162] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 263.

[163] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 270.

[164] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 199(1).

መሠረት ለቀጠሮው ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛዉ ጉድለት የሆነ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳን ፍ/ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በያዘው ቀጠሮ የመሰለውን ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ፍ/ቤቱም ምስክር ማቅረብ የነበረበት ባለጉዳይ በራሱ ጉድለት (ባለጉዳዩ ሆን ብሎ ክርክሩን ለማዘግየት ወይም በቸልተኝነት) ምክንያት ካላስመሰከረ ምስክር የማሰማት መብቱ ይታለፍበታል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተከሳሽ በጽሑፍ መልስ እና በቃል ክርክር ወቅት በሰጠዉ የእምነት ክህደት ቃል መሠረት ፍርድ ይሰጣል፡፡ ለቀጠሮዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረዉ በተከራካሪዎች ወገኖች ጉድለት ካልሆነ ግን ፍ/ቤቱ ሌላ ቀጠሮ ሊሰጥ እንደሚችል ሕጉ አመላክቷል፡፡[165] በመሆኑም ተከሳሽ በዚህ ቀጠሮ ዕለት የቀረዉ በራሱ ጉድለት (ሆን ብሎ ክርክሩን ለማዘግየት ወይም በቸልተኝነት) ያልሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ምስክሮቹን እንዲያሰማ ሌላ ቀጠሮ ሊሰጠዉ ይችላል፡፡

## 3.4. የፍ/ቤት ትዕዛዝ ለመፈፀም በተሰጠ ቀጠሮ

በኢትዮጵያ ፍ/ሥ/ሥ/ሕግ በተለያዩ የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ፍ/ቤት አንድን የተያዘ ክርክር በተገቢው ሁኔታ መርምሮ ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን እንደአስፈላጊነቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ለምሳሌ ያክል የተወሰኑትን እንመልከት፡፡ 1) ፍ/ቤት የአንድ ጉደይ ጭብጥ ከመመሥረቱ በፊት ቃላቸውን መቀበል ወይም መርምሮ ለመገንዘብ አስፈላጊ የሆኑ ምስክሮችን እና ማስረጃዎችን እንዲቀርብለት ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል፡፡[166] 2) ፍ/ቤቱ ከሌሎች ፍ/ቤቶች ወይም ከሌላ ክፍል ዘንድ የሚገኝ ሰነድ፣ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሰጠበትን መዝገብ አስቀርቦ ለመመርመር በፈለገ ጊዜ ይህ ሰነድ፣ ማስረጃ፣ ጽሑፍ እንዲቀርብለት ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል፡፡[167] 3) ፍ/ቤቱ የባለሙያ ምስክርነት ቃል ወይም ጽሑፍ ለመቀበል

---

[165] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 199(2).

[166] ዝኒ ከማሁ 249.

[167] ዝኒ ከማሁ 145.

ነገሩን የሚያውቅ ወይም ለክርክሩ ጠቃሚ የሆነ ጽሑፍ በእጁ ያለ ሰው ፍ/ቤት ተገኝቶ የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ወይም በእጁ የሚገኘውን ጽሑፍ እንዲያቀርብ በቀጠሮ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡[168] ሌሎችም ፍትህን ለማስፈን አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን እንደአስፈላጊነቱ በትዕዛዝ ቀጠሮ ይሰጣል። በዚህ የቀጠሮ ቀን ፍ/ቤቱ በትዕዛዙ መሠረት ያከናዉናል።

ሆኖም ግን በዚህ ቀጠሮ ከተከራካሪዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ካልቀረቡ ስለሚከተለዉ ዉጤት፤ ፍ/ቤት እንዲፈፀሙ ያዘዛቸው ጉዳዮች ላይ ስለሚሰጡ ትዕዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 192-199 ባሉት ቁጥሮች መሠረት መሆኑን እና በቁጥር 199(1) መሠረት ለቀጠሮው ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ሳይፈፅም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛዉ ጉደለት የሆነ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳ ፍ/ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በያዘው ቀጠሮ የመሰለውን ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡[169] ፍ/ቤቱ እንዲፈፅም የሰጠዉን ትዕዛዝ መፈፀም የነበረበት ባለጉዳይ በራሱ ጉድለት (ባለጉዳዩ ሆን ብሎ ክርክሩን ለማዘግየት ወይም በቸልተኝነት) ምክንያት ካልፈፀመ እንደሁኔታዉ በፍ/ቤቱ ይቀጣል። ለቀጠሮዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረዉ በተከራካሪዎች በአንዱ ወይም በሁለቱም ወገኖች ጉድለት ያልሆነ እንደሆነ ግን ፍ/ቤቱ ሌላ ቀጠሮ እንደሚሰጥ ሕጉ አመላክቷል፡፡[170]

## ማጠቃለያ

የሥነ-ሥርዓት ሕግ ሰዎች በመሠረታዊ ሕጎች የተደነገገዉን መብታቸውን ለማስከበር የትና እንዴት እንደሚሄዱ እንዲሁም ከአቤቱታ አቅራረብ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ደረጃ ድረስ በሚኖረው ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡ የሥነ-ሥርዓት ደንቦችን የሚደነግግ ነው። ከፍትሐ-ብሔር ክርክር ሥነ-ሥርዓት አንደኛው የፍ/ቤት ቀጠሮን ይመለከታል። ውሳኔ ላይ ለመድረስ

---

[168] ዝኒ ከማሁ 264

[169] አቶ ውርጌሳ ታደሰ v አቶ መለሰ ተካ.

[170] ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 199(2).

ሲባል ፍ/ቤት እንደአስፈላጊነቱ ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል። የሥነ-ሥርዓት ሕጎችን በተለይም ስለ ፍ/ቤት ቀጠሮና ከንዋኔ እንዲሁም ቀጠሮን አክብሮ አለመገኘት ያለውን ጉዳት ባለማወቅ ምክንያት ግለሰቦች መብታቸውን ማስከበር ሲሳናቸዉ ይስተዋላል። ይህን ለመታደግ በፍትሐ-ብሄር ክርክር ሂደት ስለሚሰጥ ቀጠሮ፣ ክንዋኔ እና ቀጠሮን አክብሮ አለመገኘት ያለውን ጉዳት ወይም የሚያስከትለዉን ዉጤት ማስገንዘብ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ሆኗል። በኢትዮጵያ ፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በቀጠሮ ቀን የፍ/ቤቶች ክንዉንን፣ ተከራካሪዎች በተወካይ ወይም ባለጉዳዩ በአካል የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ አሟልተዉ መቅረብ እንዳለባቸዉና አለመቅረባቸዉም የሚያስከትለዉን የሕግ ዉጤት ወይም ጉዳት ደንግጓል። የፍ/ቤት ቀጠሮ መሠረታዊ ዓላማ አንድን ክርክር በመመርመር ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ያለአግባብ ያልዘገየ (ቀልጣፋ) ወይም ያልተቻኮለ ፍትሕ ለማስፈን ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን ያለበት ድርጊት በተወሰነዉ ጊዜ ውስጥ ካልተከናወነ ዋጋ እንደሌለው አመላክቷል።

ውሳኔ ላይ ለመድረስ ሲባል በፍ/ቤት ከሚሰጠዉ ቀጠሮ አንዱ የክስ መልስ ለመቀበል የሚሰጥ ቀጠሮ ነዉ። በዚህ ቀጠሮ ፍ/ቤቱ ተከሳሽ የጽሑፍ መልሱን ይዞ ከቀረበ በመቀበል ጉዳዮን(ክሱ) ለመስማት ቀጠሮ ይሰጣል። ተከሳሽ መልሱን ይዞ ካልቀረበ የ default procedding ጽንሰ ሐሳብን ተግባራዊ በማድርግ በጽሑፍ የመከራከርና ተያይዘዉ የሚመጡ መብቶችን (ለምሳሌ የማስረጃ ዝርዝርና ማስረጃ ማቅረብ፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማንሳት) ያጣል፤ በክርክሩ ግን ይቀጥላል። ከሳሹ በዚህ ቀጠሮ ባይቀርብ ግን የሚመጣበት ጉዳት የለም። ሁለቱም ባይቀርቡ ግን መዝገቡ በጊዜያዊነት (struck out) ይዘጋል ወይም ፍ/ቤቱ የመሰለዉን ብይን ይሰጣል። ይህ በሆነ ጊዜ ከሳሹ ያልቀረበዉ በቂ በሚባል እክል መሆኑን በማስረዳት ያለተጨማሪ የፍ/ቤት ክፍያ ክሱ ይቀጥላል ወይም በቂ ምክንያት ከሌለዉ የፍ/ቤት ክፍያ በመክፈል አዲስ ክስ ያስከፍታል። ይህም በአንድ ጉዳይ ድጋሚ ክስ አንደቀረበ (res judicata) አይቆጠርም። ሆኖም ግን በተግባር ፍ/ቤቶች ከዚህ በተለየ ሲያከናዉኑ ይስተዋላል። ለማሳሌ ተከሳሽ መልስ ይዞ ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl

ይደረጋል፣ ከሳሽም በዚህ ቀጠሮ ካልቀረበ ክሱን መዝጋት ከጉድለቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

ፍ/ቤት የሚሰጠዉ ሌላኛዉ ቀጠሮ ጉዳዩ (ክሱ) የሚሰማበት ሲሆን በዚህ ቀጠሮ ፍ/ቤቱ ብዙ ተግባራትን ያከናዉናል፡፡ በመሆኑም የተከራካሪዎች የሁለቱም መገኘት አስፈላጊ ሲሆን ሳይቀርቡ ቢቀሩ ጠንከር ያለ ዉጤት ይከተላል፡፡ በዚህ ቀጠሮ ተከራካሪዎች ስለጉዳዩ በራሳቸዉ አንደበት ያብራራሉ፣ አንዱ ተከራካሪ ባላጋራዉ ባቀረበዉ ክርክር ላይ ግልጽ ያልሆነለትን ይጠይቀዋል፤ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ በጽሑፍ መልሱ ላይ በቀጥታ ወይም በነገሩ አካባቢ ሁኔታ እንደተካደ የሚቆጠረውን ነገር የሚያምን ወይም የሚክድ መሆኑን ተከሳሹን ወይም ወኪሉን በጥያቄ ይመረምራል፣ አከራካሪዉን ጉዳይ በመለየት ጭብጥ ይይዛል፣ በታመነዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ይሰጣል እንዲሁም ሌሎች መሰል ተግባራትን ይፈፅማል፡፡ በዚህ ቀጠሮ ተከሳሽ ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት (ex-parte) ይታያል፡፡

በመሆኑም ተከሳሽ ምስክር የማሰማት፣ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ፣ መቃወሚያ ካለ የማንሳት መብቱን ስለሚያጣ ክርክሩን የማሸነፍ ዕድሉ ይጣበባል፡፡ ከሳሽ በዚህ ቀጠሮ ባይቀርብ ጉዳዩ (ክሱ) ስለሚዘጋ (dismissal of the suit) በተመሳሳይ ጉዳይ ሌላ አዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም (የ resjudicata ፅንሰ ሐሳብና የሕጉ ቁጥር 5 ተፈፃሚ ይሆናል)፡፡ በቂ ምክንያት ካለዉና የክሱን መዘጋት ከሰማ በሠላሳ ቀን ዉስጥ የክሱ መዘጋት ይነሳልኝ አቤቱታ ካቀረበ ጉዳዩ ይቀጥላል፡፡ በቂ ምክንያት የሚባለዉ ከባለጉዳዩ ቀጥጥር ዉጪ የሆነ እና የተፈጥሮ ወይም ሰዉ ሰራሽ አደጋ ሲያጋጥም ሊሆን ይችላል፡፡ ባለጉዳዩ ሆን ብሎ ጉዳዩን ለማጓተት በማሰብ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት መሆን የለበትም፡፡ ሆኖም ግን በተግባር ጉድለቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ፍ/ቤቱ ተከሳሽ በችሎት ያልቀረበዉ መጥሪያ በአግባቡ ደርሶት መሆን አለመሆኑን ሳያረጋግጥ በሌለበት እንዲታይ ማድረግ፣ እንደ በቂ ምክንያት የሚቆጠሩ እክሎች አንዲሁም የሠላሳ ቀን የጊዜ ገደቡን አተገባበር በተመለከተ ልዩነት መኖሩ፣ ክስ ለመስማት ባለተያዘ ቀጠሮ ከሳሽ ሲቀር ጉዳዩን መዝጋት ከሚስተዋሉት ጥቂቶቹ ናቸዉ፡፡

ሦስተኛዉ ምስክር የሚሰማበት ቀጠሮ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚህ ቀጠሮ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት አከራካሪ የሆነውን ፍሬ ነገር በጭብጥ መልክ ከያዘ በኋላ አከራካሪው ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት ምስክር ወይም ማስረጃ በማስቀረብ ይሰማል፤ ይመረምራል። ማስረጃ እንዲያሰማ የተፈቀደለት ተሟጋች ምስክር የሚሰማበትን ነጥብ ለይቶ ለችሎቱ ያሰማል። በሁሉም ጭብጥ ላይ ማስረጃ መመርመር ወይም ምስክር መስማት አስፈላጊ ባይሆንም አንድ ተከራካሪ ክስ የማስረዳት ወይም የመከላከል ሕጋዊ መብት ያለው በመሆኑ ፍ/ቤት ይህን መብቱን ሊያልፍ የሚገባው ተከራካሪዉ ወገን የቆጠረው ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን እርግጠኛ ሲሆን ብቻ ነዉ። ነገር ግን በተግባር ፍ/ቤቶች ከዚህ በተለየ መልኩ ተሟጋቹ ስለቆጠረዉ ማስረጃ አግባብነት ምንም ሳይሉ የተሟጋችን ማስረጃ በዘፈቀደ ሳይቀበሉ ማለፍ ተጠቃሽ ጉድለት ነዉ። ተከራካሪ ወገን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ ቆጥሮ እያለ ማስረጃ ሳይሰማ ፍርድ መስጠት የመከራከር መብቱን የሚያጣብብ ነው፣ ውሳኔውም ሕጋዊ ሥርአቱን ተከትሎ ተሰጥቷል ሊባል የሚችል አይደለም።

በተጨማሪም ምስክሮችን በመስማት ሂደት በከፊል ፍ/ቤቶች ምስክር ከመጥራታቸዉ በፊት ጭብጥ አለመያዛቸዉ የማስረዳት ሸክም ማን ላይ እንደሚወድቅ አለመለየት፣ ባለጉዳዮች የሚጠሩዋቸዉ ምስክሮች በሙሉ የመጥራትና ጭብጥ ባልሆነ ጉዳይ ላይ እንዲመሰክሩ ማድረግ፣ ምስክር የሚሰማዉ በተለያየና በጣም በተራራቀ ጊዜ መሆኑ፣ የአንዱ ወይም የሌላዉ ምስክር ተሟልቶ አልቀረበም እየተባለ የሚሰጠዉ ተጨማሪና ተደጋጋሚ ቀጠሮ እና ለምስክሩ በቂ አበል አለማስያዝን በሚመለከት በተግባር ካሉት ችግሮች እንደምሳሌ ይነሳሉ። ተከሳሽ ምስክር እንዲያሰማ በታዘዘበት ቀጠሮ ካልቀረበ ምስክር የማሰማት መብቱን ያጣል። በዚህ ቀጠሮ ከሳሽ ካልቀረበ የተከሳሽ ምስክሮችን ቃል በመስቀለኛ ጥያቄ ማስተባበልና በምስክር መስማት ሂደቱ ላይ መቃወሚያ የማንሳት መብቱን ያጣል። ከሳሽ ምስክር እንዲያሰማ በታዘዘበት ቀጠሮ ካልቀረበ ምስክር የማሰማት መብቱን ያጣል። በዚህ ቀጠሮ ተከሳሽ ካልቀረበ የከሳሽ ምስክሮችን ቃል በመስቀለኛ ጥያቄ ማስተባበልና በመስክር መስማት ሂደቱ ላይ መቃወሚያ የማንሳት መብቱን ያጣል።

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl

ጠቅለል ባለ መልኩ በፍትሐ-ብሄር ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ፍ/ቤቱ የሚሰጠዉ ቀጠሮ የተከሳሽን መልስ ለመቀበል፣ ክሱን ለመስማት ፣ ክርክር ለመስማትና ምስክሮችን ለመመርመር፣ ማሰረጃ መርምሮ ተገቢውን ትዕዛዝ ለመስጠት፣ በሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ የሌላኛውን ወገን አሰተያየት መቅረብ ለመጠባበቅ፣ ያልቀረበ ማስረጃ እንዲቀርብ ለመጠባበቅ፣ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ፍርድ ለመስጠት ዓላማ የሚሰጥን የቀጠሮ ያጠቃልላል። የተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱ እንደየሁኔታዉ በተሰጠዉ ቀጠሮ አለመቅረብ ከሚያስከትለዉ ዉጤት መካከል መልስ በጽሑፍ የማቅረብ መብት መታለፍ (default proceeding) ፣ ማስረጃ ወይም ምስክር የማሰማት፣ መስቀለኛ ጥያቄ እና መቃወሚያ የማንሳት መብት መታለፍ ፣ የመዝገብ መዘጋት (struck out) የክስ(ጉዳዩ) መዘጋት (dismissal)፣ ተለዋጭ ቀጥሮ መስጠት እና ተከሳሽ በሌለበት ለቀጠሮዉ ምክንያት የሆነዉን ጉዳዩ መስማት መቀጠል (ex-parte proceeding) ናቸዉ።

ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሚያስብሉት ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ሕጉ አልጠቀሰም። ይልቁንም ሕጉ በስራ ብዛት፣ በመዘንጋት፣ በቸልተኝነትና በራሱ ጉድለት (ባለጉዳዩ ሆን ብሎ ክርክሩን ለማዘግየት ወይም በቸልተኝነት) መሆኑ በታወቀ ጊዜ እንደ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት እንደማይቆጠርና አዲስ የጊዜ መራዘም ዉሳኔ እንደማይሰጠዉ ያስገነዝባል። ፍ/ቤቶችም እንደ በቂ ምክንያት የሚቆጠረዉን ጉዳይ ለመለየት ሲቸገሩ ይስተዋላል። በፍ/ቤቶች በተግባር በቂ ምክንያት ናቸዉ ከተባሉት ዉስጥ በጠበቃ መቀየር ምክንያት ጠበቃ ለባለጉዳዩ ሳያሳዉቅ ዉሉን መሰረዙ፣ መንገድ መዘጋጋት፣ በራሱ ባልሆነ ችሎት ተሳስቶ ገብቶ በእሱ ችሎት አለመገኘት ይጠቀሳሉ። በቂ ምክንያት እያለዉ መዝገብ የተዘጋበት፣ ከስ (ጉዳዩ) የተዘጋበት እና በሌለበት ክሱ የተወሰነበት ተከራካሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 71፣ 74፣ 78 የተመለከቱትን መፍትሔዎችን በቅደም ተከተል በመጠቀም መብቱን ማስከበር ይችላል።

ሕጉ በቀጠሮ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ወይም ሁለቱም ፍ/ቤት በያዘው ቀጠሮ አለመገኘት ስለሚያስከትለው ውጤት ቢደነግግም ክፍተት የለበትም ማለት አይቻልም። ለምሳሌ፡ የሕጉ የአማረኛ እና የእንግሊዘኛዉ ቅጂ ልዩነት፣ ግልፅነት መጉደል፣ ክስ ለመስማት ከሚሰጥ ቀጠሮ ዉጪ በሌሎች ቀጠሮዎች የተከራካሪዎች መቅረትን በሚመለከት ግልጽ ድንጋጌ አለመኖር እና ለትርጉም የሚጋለጡ ቃላቶች መጠቀሙ (ለምሳሌ 'በቂ ምክንያት'፣ 'በራሱ ጉድለት') እንደ ክፍተት ማንሳት ይቻላል። ሕጉ ከስልሳ አመት በላይ ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ በሆነዉ ጉዳይ ላይ ማሻሻያ አለመደረጉ ችግሩን ያባብሰዋል። ይህን የሕጉን ክፍተት ለመቅረፍ ሕጉን ማሻሻል አንዱ የእረጅም ጊዜ መፍትሔ ነዉ። በፍ/ቤቶችም በኩል በክርክር ሂደት ከሕጉ በተለየ መልኩ መተግበራቸዉ ጉልህ ችግር ነዉ። ከእነዚህም መካከል ፍ/ቤት በሚሰጠዉ ቀጠሮ የሚተገብረዉ ክንዋኔ፣ በቀጠሮ ባልቀረበ ተከራካሪ(ዎች) ላይ የሚወስደዉ እርምጃ በተደጋጋሚ ከሕጉ ዉጪ መሆኑ እንደምሳሌ ይጠቀሳል። ይህ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ኢኮኖሚያዊ የፍትህ ሥርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፤ የዜጎችንም ሕጋዊ መብት ያሳጣል።

በመጨረሻም ሁሉም የፍትሐ-ብሄር ክርክር ባለጉዳዮች የፍ/ቤት ቀጠሮ (ቀን እና ሰዓት) በማክበር እንደ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መፈፀም እንዳለባቸዉና አለማክበራቸዉ የሚያስከትለዉ ጉዳት እንዳለ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ጉዳዩን ለማየት የተሰየመው ፍ/ቤትም ነገሩን ላለማጓተት እና ፍትህን ለማረጋገጥ በፍ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕግ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው የሕግ ትርጓሜ መሠረት ተገቢውን ሥነ-ሥርዓት በመከተል ውሳኔ ላይ መድረስ ይኖርበታል።

ISSN: 2664-3979
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl